ቅንነት ድል ያደርጋል!

መስከረም-5-2013

# ቅንድል

ዲጂታል መፅሔት



"...
ሴቶችን ከማስተማር
ጎን ለጎን የተማሩ ሴቶችን
የሚቀበል ማህበረሰብ
ማዘጋጀት ግድ
ይለናል።..."

አርቲስት ሳያት ደምሴ

ልዩ የበአል እትም

ቅፅ-፩ ቁጥር-፫

**ምኞት ያሰከረው የሰው ልጆች የዘመን መለወጫ**


✍ ነዋል አቡበከር

**የቢጫ ወርቅ ሀገር ... እንቁ ...ጣጣሽ**

✍ በሀይሉ ወ/ይፍራው

**የአዲስ ዓመት ዕቅድ ስነ-ልቦና**

✍ፈራኦል መስፍን




እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ!
ቀንድል ዲጂታል መፅሔት ለመላው
ኢትዮጲያውያን አዲሱ ዓመት የሰላም፣
የፍቅር፣ የደስታ፣ የመቻቻል እና የአንድነት
እንዲሆንላችሁ ይመኛል፡፡ጥላቻን፣ ቂምን፣
መገፋፋትን፣ መለያየትን በቅንነት ፣
በምክንያታዊነት እና በይቅርታ ድል አድርገን
በአንድነት ወደ ህልማችን ጫፍ የምንሮጥበት
የድል ዓመታችን ነው፡፡

እንቁጣጣሽ!



ቅንድል
DIGITAL MAGAZINE

# ማውጫ




04 ርዕሰ-አንቀፅ

06 የቢጫ ወርቅ ሀገር እንቁጣጣሽ
ሀገሬ
በሀይሉ ወንድይፍራው

09 የአውደብሩሀን ገፃች
ቆይታ ከሳያት ደምሴ ጋር

15 የቅኖች ገፅ

18 ምኞት ያሰከረው የሰው ልጆች ዘመን መለወጫ
አጀኢብ
በነዋል አቡበከር

20 የአዲስ አመት እቅድ ስነልቦና
አዕምሮ ጤና
በፊራኦል መስፍን

28 እንኳን አደረሳችሁ
ንንሳ አወት
በአናናስ ግርማይ

30 እልፍ ገፃች
በ ዮናስ ሀ/ማርቆስ

35 የ2012 ሳይ ቴክ ሪፖርት
ሳይ-ቴክ
በ ለአለም ክንፈ



ልዩ የበአል እትም
ቅንድል | ቅንነት ድል ያደርጋል!

POWERED BY
ESQUARE

# ርዕሰ - አንቀፅ

## "የድል አመት"

ድል አልያም ማሸነፍ የሚለው ቃል ሲነሳ ብዙዎች አንዱን ጥሎ ከማለፍ ፣ ከጦርነት ማሸነፍ ፣ ተደባድቦ ከመጣል ጋር ያገናኙታል።
ጠቢቡ ሰለሞን በታላቁ መፅሐፍ ላይ ''...ኃይለኛ ከመሆን ይልቅ ታጋሽ መሆን ይሻላል ፤ ብዙ ከተሞችን በጦርነት ድል ነስቶ ከመያዝ ይልቅ ራስን መቆጣጠር ይበልጣል''(ምሳ.16:32) ይለናል!
ታድያ በዚህ ቃል ላይ ጠቢቡ ሰለሞን ድል ማድረግ አልያም ማሸነፍ ራስን ቀድሞ ከማሸነፍ እና ከመግዛት እንደሚጀምር ያስረዳናል።
ታድያ እኔም ዛሬ 2013ን የድል ዓመት ነው ስል ራሳችንን በመግዛት ስለምንቀዳጀው ትልቅ ድል ነው። ድል ማድረግ ማለት በአንዲት ነጠላ ስኬት የሚዳሰስ ሳይሆን በሁለንተናዊ የህይወት አኗኗር ድምር ውጤት የሚለካ ሁነት ነው። ለዚህም ይመስላል ዶ/ር ዴኒስ ዌትሊ The psychology of winning በሚለው መፅሀፋቸው "ድል ማድረግ የሕይወት አኗኗር ነው" ያሉት።
በሳለፍነው ዓመት ራሳችንን ባለመግዛታችን በኢምክንያታዊነት እና በስሜታዊነት የብዙ ሰዎችን ህይወት አጥተናል ፣ ከምንወዳቸው ሰዎች ጋር ተጋጭተናል ፣ ስራዎቻችን ተበላሽተዋል ፣ የሕይወት አኗኗራችን ቅጥ አጥቷል .... ወዘተ በውጤቱም መድረስ ከነበረብን ከፍታ ሳንደርስ የመለወጥ ውጥናችን እንዲሁ ምኞት ብቻ ሆኖ ቀርቷል። አልፎም በህይወታችን ሙሉ የሆነ ደስታን አጥተናል።
በአዲሱ ዓመት ታድያ 'ምንም ነገር ስሜቴን እንዲቆጣጠር አልፈቅድም!' በማለት የእለት ተእለት እንቅስቃሴያችንን ፣ ማህበራዊ መስተጋብራችንን ፣ ስራዎቻችንን በቅንነት በምክንያታዊነት እና በሀገር ፍቅር እሳቤዎች በመስራት ሁለንተናዊ ድል ማስመዝገብ እንችላለን።
2013 ጥላቻን ፣ ክፋትን ፣ መለያየትን ፣ የበላይነት እና የበታችነት ስሜትን በመግዛት እና በመቆጣጠር በአብሮነት ወደ ራዕያችን ከፍታ የምንሮጥበት የድል ዓመት ይሁንልን።



ቅንድል ዲጂታል መፅሔት በቅንድል ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ማህበር ወጣቶች ተዘጋጅቶ በ E-square አድቨርታይዚንግ እና ኢቨንትስ የሚቀርብ በማህበራዊ፡ ስነልቦናዊ እና ጤናነክ ጉዳዮች ዙርያ የሚያተኩር ዲጂታል መፅሔት ነው።
የካቲት 2011 ተቋቋመ።


✔ አድራሻ
✆(+251)912178520
✆(+251)920019699
e-mail- kdigitalmagazine@gmail.com




**አዘጋጅ**


በሀይሉወ/ይፍራው ( መባ)
e-mail- ethiomebreku3000@gmail.com
Telegram-@Dasolo
✆(+251)924140293




**አዘጋጅ**


ነዋል አቡበከር
e-mail-newalabubeker13@gmail.com
Telegram-@entisar13
✆(+251)937683378




**ም/አዘጋጅ**


ነፃነት ጌታቸው
netsanetg43@gmail.coment
Telegram-@mistretigist
✆(+251)953498678




**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**


ኤርሚያስ ደጀኔ
e-mail-ermiyasdejene@gmail.com
Telegram-@jeremy00
✆(+251)912178520




**አርታኢ**


አወት ሀይለስላሴ
e-mail-awoth12@gmail.com
Telegram-@Awicha12
✆(+251)920152581


**የመፅሔት ዲዛይን**


MHgraphics
e-mail-EsruMH1@gmail.com
Telegram-@MHgraphics
✆(+251)920019699




**አርታኢ**


ቀለዮጳ ደስታ
e-mail-cleopadada2012@gmail.com
Telegram-@adadada8
✆(+251)941535884




**ማርኬቲንግ**


ዮናስ ጎ/ማርቆስ
e-mail-lijyoha2@gmail.com
Telegram-@Yonas_H
✆(+251)970514616




**አርት ዳይሬክተር**


ፍራኦል መስፍን
firaolmesfin8@gmail.com
Telegram-@forgiven247
✆(+251)923602445




**ማርኬቲንግ**


ያሬድ ለማ
e-mail-Yaredlemma487@gmail.com
Telegram-@Yared4444
✆(+251)932540523


ቅንነት ድል ያደርጋል!

በሀይሉ መድይፍራው(መ)
በድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ የማኔጅመንት መምህር እና
ቢዝነስ ሪሰርቸር
ethiomebreku3000@gmail.com




# የቢጫ ወርቅ ሀገር
# እንቁ...ጣጣሽ

የቢጫ ወርቅ ሀገር የዘመን ስጦታ
ጭጋግ ወራት አብሪ አድማቂ በልልታ
ዘመን መቶልሻል ዘመን አዲስ አመት
ካለፈው የፈካ የሚኖር በምህረት።

የግዜ አቆጣጠር የሰው ልጅ ተፈጥሮን ከማስተዋልና አጠቃላይ የጨረቃን ፣ የምድርን ፣ የፀሀይን እና የከዋክብት ቁርኝት በጥብቅ በመከታተል የቀመረው ሆኖ እናገኘዋለን። የሰው ልጅ በዙሪያው ያሉት የህዋ አካላትና የተፈጥሮ ወቅቶችን በመደበኛነት መቀያየር ተከተሎ የግዜ ቀመርን መበየን ችሏል። ይህም የጨረቃን እንቅስቃሴ እንደዚሁም የምድርን ዙረት ተከትሎ የጀንበርን መጥለቅና መውጣት በጥልቀት ከማስተዋል የመነጨ ነው። ሰዓታትን ወደ ቀናት ቀናትን ወደ ወራት ከዚያም ወደ አመታት አስልቶ በመቀመር የግዜ አቆጣጠርን መፍጠር ችሏል። በዚህም መሰረት በአለም ላይ የጨረቃን ዙረት በመከተል የተቀመረ የግዜ አቆጣጠር (lunae calendar) በመባል የሚታወቅ ሲሆን ሌላኛው የምድርን በፀሐይ ዙሪያ መሽከርከር ተከትሎ የተቀመረው የፀሐይ የግዜ አቆጣጠር( solar calendar) በመባል ሲጠራ ሶስተኛው ቀመር እነዚህን ሁለት የግዜ አቆጣጠር አጣምሮ የተገኘው ( lunesolar calendar) በመባል ይታወቃል ።

ሰላም የተወደዳችሁና የተከበራችሁ የቅንድል ዲጂታል መጽሄት የሀገሬ አምድ እንባቢያን እንደምን ቆያችሁኝ .......ሳምንታቶቹ የሰላም ፣ የመተሳሰብ ፣ የቅንነት ፣ የምክንያታዊነት መሰረት እንደነበሩ ሙሉ እምነቴ ነው።

በዛሬው የሀገሬ አምድ የበዓል ልዩ ዕትም ወደናንተ ላደርስ የወደድኩት ርዕሰ ጉዳይ አዲስ አመት እንደመሆኑ ስለ ሀገራችን የዘመን ቀመር አመቆጣጠር መሰረት ከአለም ሀገራት ጋር በማያያዝ የ13 ወር ፀጋ ባለቤት ስለሆንበት ሚስጥርና በዓሉን ስናከብር ምን መሆን አለበት በሚል ሀሳቤን ወደናተ ለማድረስ ወደድኩ።

አለም ላይ የራሳቸው የዘመን አቆጣጠር ያላቸው ሀገራት ፣ ብሔሮችና ጎሳዎች ያሉ ቢሆንም በዋነኝት አለም የሚያውቃቸው አራት እንደሆኑ በተለያዩ የሐይማትና የታሪክ መዛግብት ተጽፎ ይገኛሉ። እነሱም፦ የጎርጎሮሳውያን የዘመን አቆጣጠር ፣ የአይሁዳውያን የዘመን አቆጣጠር ፣ የአረቦች ዘመን አቆጣጠር እንዲሁም የሀገራችን የኢትዮጲያ ዘመን አቆጣጠር ሚጠቀስ ነው። እነዚህ በዋነኝነት በዓለም ሀገራት ይታወቁ እንጂ በአንድ ሀገር ውስጥ እንኳን በርካታ ጎሳዎች የተለያዩ የዘመን አቆጣጠር አላቸው። ለምሳሌ በሀገራችን የሲዳማ ብሄር የዘመን መለወጫ ፍቼ ጨምበላላ ፣ የወላይታ ጊፋታይ እና ሌሎችም ተጠቃሽ ናቸው።

ከአራቱ የዘመን አቆጣጠሮች ውስጥ አይሁዳውያን የሚከተሉት ቀመር የጸሀይን እና የጨረቃን በአንድ ያያዘውን ሉኒሶላር ሲሆን አብዛኞቹ የመካከለኛው ምስራቅ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ሀገራት ከጥንት ጀምሮ የሚጠቀሙበት የዘመን ቀመር የጨረቃን ዙረት በመከተል ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ግን የአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር ( ግሪጎሪያን ካላንደር) በመከተል የጥንቱን ለሀይማኖታዊ ስርዓት ብቻ በማዋል ላይ ይገኛሉ።

የጨረቃ አቆጣጠር በአንድ ወር ውስጥ 29 ቀናት ከ12 ሰዓታት ከ44 ደቂቃዎች ከ3 ሰከንድ አካቶ የያዘ ነው። ይህ አቆጣጠር ወራቱን የሚቆጥረው 29 እና 30 ቀናት በማፈራረቅ ነው። በዚህም መሰረት 6 ባለ 29 ቀናት 6 ባለ 30 ቀናት አሉት። የጨረቃ አመት በውስጡ 354 ቀናትን 8 ሰዓታትንና 48 ደቂቃዎችን ከ 34 ሰከንድ አካቶ የያዘ ነው። ሌላኛው ጸሀይን መሰረት ያደረገው የግዜ አቆጣጠር(solar calendar) የተቀመረው ምድር በፀሐይ ዙሪያ አንድ ግዜ ለመዞር የሚፈጅባትን ግዜ በማስላት ነው። ምድርን ፀሐይን ለመዞር ከአንድ መነሻ በመነሳት ወደ ነበረችበት ለመመለስ 365 ¼ ቀናት ይፈጅባታል። በዚህም መሰረት በሁለቱ የግዜ አቆጣጠር መሰረት የ11 ቀናት ልዩነት አለ።

ይህን መነሻ በማድረግ የሀገራችን ኢትዮጲያ የዘመን አቆጣጠር መሰረት ያደረገው የምድርን በፀሐይ ዙሪያ (ኡደታዊ )እንቅስቃሴ የሚከተል ነው በማለት የሳይንስ ጠበብቶች ሲያስቀምጡ በሌላ በኩል የሀይማት ድርሳናትና አባቶች የሀገራችን የዘመን ቀመር የሚጀምረው አለም ከተፈጠረችበት ግዜ ጀምሮ ከስነ ፍጥረት ጋር የተያያዘ ነው በማለት ያስረዳሉ። ታዲያ ከዚህ ግዜ ጀምሮ ሳድሲቱ፣ አምስት ፣ አምሲቲ ፣ ራብዒት ፣ ራብዒቱ ሳልሲት ፣ ሳድሲቱ ክልኢት ፣ ካልኢቶ ኬክሮስ ፣ ኬክሮሱ ሰዓታት ፣ ሰዓታቱ ሳምንታት ፣ ሳምንታቱ ወራት ፣ ወራቱ አመታት ፣ አመታቱ አዝማናት እየሆኑ ዛሬ ካለንበት እንደደረስን አበው በድርሳናት ያስረዳሉ ። ሳድሲት ፣ አምሲት ፣ራብኢት… ወ.ዘ.ተ ተብለው የተገለጹት በአሁኑ አነጋገር ማይክሮ ሰከንድ ፣ ሰከንድ እንደሚባሉ እጅግ በጣም ደቃቅ የሆኑ የግዜ መለኪያዎች ናቸው። ታዲያ አለም ወደ አንድ የግዜ ቀመር የመጣው ጁሊየስ ቄሳር በቀመረው የጁሊያን ቀመር ነው። ይህ አይነቱ የግዜ ቀመር አቆጣጠር መሰረቱ የምድርን በፀሐይ ዙሪያ በሚደረግ ኡደት መሰረት በማድረግ ነው። ይህ የግዜ ቀመር በምዕራባውያን ጥናትና ምርምር ግድፈት ተገኝቶበት እንዲቀየር የተወሰነ ሲሆን የምዕራብ አውሮፓ ሀገራት የቀመሩት አዲሱ የግዜ ዘመን አቆጣጠር አቆጣጠሩ እንዲለወጥ ባደረገው የካቶሊኩ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ግሪጎሪ 8ተኛ በ1582 ዓመተ ምህረት ተቀይሮ በሱ ስም እንዲጠራ የተወሰነ ሲሆን አሁን ከኢትዮጲያ ውጭ ያለው አለም 2020 G.C (ግሪጎሪያን ካላንደር ) በማለት እየተጠቀሙበት ይገኛሉ።

አቡነ ግሪጎሪ የዘመን ቀመሩ እንደገና እንዲሰላ በወሰነበት ወቅት በአንድ አመት ውስጥ 365 ቀናት ከ 6 ሰዓት ነው ያለው በማለት በየአመቱ አንድ አንድ ሰዓት እንዲጨመር ወስኖ ከ325 ዓ.ም ጀምሮ ያለው ግዜ እንዲሰላ በማድረግ 10 የተዘለሉ ቀናት መኖራቸውን በማቅረብ በግዜው በነበረው ቀን ላይ 10 ቀን በመጨመር ከቀናት ባለፈ የአመቶች ልዩነቶችን በመጨመር በጁሊያን ቀመር ላይ በመደመር የ8 አመታት ልዩነት እንዲፈጠር አድርጓል።

ነገር ግን ይህንን የግሪጎሪያን የዘመን ለውጥ ያልተቀበሉት ሁለት ሲሆኑ እነሱም የምስራቅ ኦርቶዶክስ እና የኦሬንታል ኦርቶዶክስ ተከታይ ሀገራት ሲሆኑ በበፊቱ የጁሊያን ዘመን አቆጠጠር መቀጠል መርጠዋል። በግዜ ሂደት ከኢትዮጲያ ውጭ ያሉት ሀገራት የጁሊያንን የዘመን አቆጣጠር ለሀይማኖት ብቻ በማድረግ የግሪጎሪያንን ሲከተሉ ሀገራችን በዛው ቀመር እስካሁን ድረስ ቆይታለች ። ይሁንና ከዚህ ሳይንሳዊ ትንታኔ ውጭ ያሉ የሀይማኖት መጻሐፍትና ሊቃውንት እንደሚሉት የኢትዮጲያ የዘመን አቆጣጠር ከጎርጎሮሳውያኑ በ8 ዓመት የዘገየው አዳም በገነት ቆይቶ ዕጸ በለስን በልቶ ወደ ምድር ሲወርድ እና ቦሀላም በመፀፀት ሱባኤ በመግባት ከፈጣሪው የተስፋ ቃል ከተሰጠበት ዕለት ጀምሮ ስለምትቆጥር ነው። አዳም በገነት የቆየባቸው 7 አመታት ከአንድ ወር ከ17 ቀን የደስታ ግዜ ስለነበሩና የአዳም ዕድሜውና ዘመኑ መቆጠር የጀመረው የተስፋ ቃል ከተሰጠበት ግዜ ጀምሮ ስለሆነ ኢትዮጲያም አዳም ዘመን የቆጠረበትን መሰረት አድርጋ ዘመን ቆጠረች በማለት ያስረዳሉ ይሁንና ስለዘመን ቀመር ስናነሳ የምናገኘው ዕውነት እስካሁን የተጠቀሱት ናቸው ። በዚህም አውሮፓውያኑ እና የቀረው አለም ጥር 1 የዘመን መለወጫ ሲከብር እኛ ኢትጲያውያን መስከረም 1 እናከብራለን። የሀገራችን ሁሉም ወራት 30 ቀናት ሲኖራቸው የቀረው ጳግሜ ወር 5 ¼ ቀን በመሆን የ13 ወር ጸጋ ያላት ሀገር ብሎ አለም ያወድሰናል።

ውድ እንባቢያን ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ስለሀገራችን የዘመን አቆጣጠር አመጣጥ ይህን ያህል ካልኩ የቢጫ ወርቅ ሀገር የሆነችው ኢትዮጲያ እንቁ የሆነውን በአርንጓዴ ምድር ላይ የበቀለ ቢጫ አበባ አስውባ መስከረምን ስትሰጠን እኛስ እንቁ ሆነን ጣጣን ጥለን እንዴት እንቀበለው ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው።

ለአዲስ አመት አዲስ ለብሰን ፣ ተስፋ ሰንቀን ፣ ፍቅር አኡረን ፣ መልካምነትን ተግብረን የምናከብረው ብቻ ሳይሆን አዲስ ስንለብስ ካለን ላይ ለተቸገሩት የምናካፍልበት ፣ በፍካት ስንስቅ በአዕምሯችን የተሞላውን ክፋት ፣ ዘረኝነት ፣ ጥላቻ ፣ ቂም ወደ ኋላ ጥለን እኛ ሞልቶ ተርፎን ጠግበን ስንደፋ ምንም የሚቀመስ ላላገኙ በየጎዳናው የወደቁትን የምናስብበት ዘመን ፣ የሀሳብ ፣ የኑሮ ፣ የትምህርት ፣ የህይወት መንገድ ለውጥ የምናደርግበት አመት መሆን ይገባዋል።

በትናንት ቁርሾ ፣ በደል ፣ ቂም የነገን ብርሀን የምንቀበልበት ሳይሆን በፍቅር፣ በአንድነት ፣ በመቻል ፣ በቅንነትና በህብረት የምንመራረቅበት ይሁንልን። አዎ አሜን እያልን ሀገርን ፣ አሜን እያልን እማማን ፣ አሜን እያልን ጋሼን ፣ አሜን እያልን እታለምን ፣ አሜን እያልን የሰው ልጅን ሁሉ የምንመርቅበት እንዲሆን በምርቃት ልጀምር።

አዎ አሜን በይ እማማ
የልጆችሽ ተስፋ ፣ የሀገርሽ ህልም ፣ የህይወትሽ ተድላ የሚሞላት ያድርግልሽ
አሜን በል ጋሽዬ
አፈሩን ቆርሰህ የዘራህው ፣ ዝናብ እየደበደበህ ያኖርከው ትሩፋትህ
ብልጽግና ላንተ ፣ ጥጋብ ለሀገሬው ፣ ተድላ ለትውልድህ የሚያድል አመት ያድርግልን
አሜን በል ያገር ሰው አሜን በል ተስፈኛው አሜን በል ወጣቱ
አንተ የነገ ባለቤት ፣ እደጅ አድራለው ኮከብ ስቆጥር የሚለውን የተስፋ ቃል በልብህ አኡሮ ዘር መቁጠር ያጥፋልህ ፣ ተከፍተህ የምታልፈው ሳይሆን ኖሮህ የምትሰጥበት ዘመን ይስጥህ።
አሜን በይ እታለም አሜን በይ እንስቱ
ዘመንሽ ይባረክ ከወጪ ያድንሽ
ስቀሽ የምታልፊው ውብ ዘመን ያድልሽ
ኖሮሽ የምትሰጪ ወርቅ እንስት ያድርግሽ
አሜን በይ ሀገሬ

ምድርሽን ከአደይ የበለጠ ምን አይነት አበባ ሊወክላት ይችላል? ከመስከረም የበለጠ ወርስ ምን አለሽ ? በቢጫ ቀለም የያዘች ውብ አርንጓዴ ምድርሽን በቀይ ደም ተቦክቶ በተቀበረ መሬት የበቀሉ ልዩ ስጦታዎችሽ ናቸውና አሜን በይ ሀገሬ።

የስምሽ ትርጓሜ ከተሰራባቸው አንዱ ‹ዮጵ› ትርጓሜው ቢጫ ወርቅ ማለት ነውና ቢጫ ፀሐይ ነው፣ፀሐይ ከሌለ ህይወት ስለሌለ መጪው ዘመንሽ እንደ ፀሐይ የፈካ ፣ ልጆችሽ እንደ ወርቅ የከበሩ በህብረት የሚሰሩ ፣ በአንድነት የሚኖሩ ያርግልሽ። አሜን በይ ሀገሬ!

ይህንን ሁሉ ምርቃት ሳወርድ አንድ ነገር ትዝ አለኝ በአዲስ አመት ሁሉም ማለት በሚቻል መልኩ ዕቅድ ያወጣል ግን ዕቅዳችን ምን ያክል ይሰራል የሚለውን የሚያመዛዝነው ምን ያህሉ ሰው ነው ስል በዚሁ ሀሳቤን አሳሁ። እንደ ትንቢት ዘርግፈን በገዛ እራሳችን ላይ በቀለልነው ለከት የለሽ ዕቅድ ምክንያት ደስታችንን መነጠቅ የለብንም። ስለዚህ ዕቅድ ዶሮ አፈጻጸም ሽሮ እንዳይሆንብን አቅማችንን መሰረት ያደረገ ዕቅድ በማውጣት እና በመፈጸም መጪውን አመት በመተሳሰብ ፣ በመዋደድ ፣ በቅንነት ፣ በምክንያታዊነት ፣ በሀገር ፍቅር ደምቀን ራሳችንን ፣ቤተሰባችንን ብሎም ሀገራችንን ኢትዮጲያ ወደ ከፍታ ማማ የምናደርስበት ዘመን ያድርግልን እያልኩ የአዲስ አመት የሀገሬ አምድ ጽሁፌን አበቃሁ።

መልካም በዓል!

አንደ ምድሩ የፈካ ፣ እንደ ወራቱ ያበራ የድል ዘመን ያድርግልን!
ኢትዮጲያ ለዘላለም በህዝቦቿ ፍቅር ትኑር...





# #የአውደ ብሩሀን ገፆች

ሰላም የተከበራችሁ እና የተወደዳችሁ የቅንነት ዘማሪ ፣ የምክንያታዊነት ምልክት ፣ የሀገር ፍቅር ማሳያ የሆናችሁ ባለራዕይ የቅንድል ዲጂታል መጽሄት አንባቢያን እና የቅንድል ኢትዮጲያ ቤተሰቦች። እንደሚታወቀው በአውደ ብሩኃን ገጻችን በሀገራችን ኢትዮጲያ በኪነ-ጥበብ ፣ በትምህርት ፣ በጤና ፣ በማህበራዊ ግልጋሎት ፣ በበጎ አድራጎት ፣ በስፖርትና በሌሎች የተለያዩ የሙያ ዘርፎች  ለሀገራቸው በርካታ ትሩፋትን ያበረከቱና ቅንነትን መለያቸው ፣ ምክንያታዊነትን የህይወት መርህ አድርገው በሀገር ፍቅር ከተቃኙ መካከል ለናንተ ለአንባብያን በተለይም ለወጣቶችና ለሴቶች ከህይወታቸው ፣ ከስብዕናቸው ፣ ከስራ ውጣ ውረዳቸውና ከትዝብታቸው ትማሩበታላችሁ ያልናቸውን ወደናንተ የምናደርስበት አምድ ነው። ታዲያ በዛሬው የዐውደ ብሩኃን ገጽ እንግዳችን በኢትዮጲያ የፊልም ዘርፍ በአዲስ የአተዋወን ዘይቤ ቀልባችንን በሳበው ‹‹ ስላንቺ››ፊልም አሀዱ ብላ ፣ በሀገር አቀፍ የቁንጅና ውድድ የሞዴልንግ ስራ በውበት ብቻ ሳይሆን በስብዕና እና በእውቀት አሸናፊነትን የተቀዳጀች ፣በሙዚቃው ዘርፍም በልዩ ለዛ የወጣቶችን ቀልብ የገዛችው እንዲሁም በታላቁ የአፍሪካውያን ቤት በሆነው የአፍሪካ ህብረት ባላት የመልካምነት ፣የምክንያታዊነት ፣ የሀገር ፍቅር ስብዕና እምነትና ሀላፊነት ተጥሎባት የወጣቶች አምባሳደር በመሆን እያገለገለች የምትገኘውና ለሴቶች ጤናና እኩልነት በሁሉም መድረክ የምትሟገተው ሁለገቧ የኪነ-ጥበብ ሰው ሳያት ደምሴ የዛሬው የአውደ ብሩኃን ገጽ እንግዳችን ናት።

በመሆኑም እኛም ከማንነቷ ፣ ከህይወት ትሩፋቶቿ ፣ ከግል የስራ አለም ስኬቷ ፣ ትምህርቷና ፈተናዋ ትማሩበታላችሁ ብለን ስላሰብን እንደሚከተለው ቆይታ አድርገናል።

ቅንድል፡- ሳያት ጥሪያችንን አክብረሽና ፍቃደኛ ሆነሽ ለአንባቢያን እና ለሀገራችን ወጣቶች ዘርፈ ብዙ የሆኑ ተሞክሮዎችሽን ልታካፍይን ስለ ተገኘሽ በቅንድል መጽሔት አንባቢያን እና በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ እናመሰግናለን።

ሳያት፡- እኔም እጅግ በጣም አመሰግናለሁ ። የምትናገረው ና የምትለው አላት ብላችሁ አክብራችሁ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ ።

ቅንድል፡- ሳያት እንግዳችን በመሆን ስለተገኘሽ በድጋሜ ከልብ እናመሰግናለን! በቀጥታ ወደ ቀዳሚው ጥያቄ ላምራና ሳያትን ብዙ ግዜ በስራዎቿ ፣ በሙያዋ ትታወቃለች ግን ከነዚህ ውጪ በሰውኛ ባህሪዋ  ለሚያውቋትና በደንብ ለማያውቋት ማናት የሚለውን በደንብ ብታካፍይ ወይም ሳያት ደምሴ በጥቅሉ ማናት?

ሳያት፡- እእእእ እኔንጃ ያው ሰው የራሱን ሃሳብ እንዲ ነኝ ብሎ ለመናገር ይከብድ የለ? ግን ከጠየቅሽኝ ለመመለስ ልሞክር ሳያት ቀጥተኛ ነች። ሃሳቧን በቀጥታ የምገልፅ እንዲሁም ችግሬንም ሆነ መናገር የምፈልገውን ነገር ሁሉ በግልፅ የምናገር አይነት ሰው ነኝ ብዬ አስባለሁ።

ቅንድል፡ ሳያት በጥበብ ሙዚቀኛና ተዋናይ ፣ በሙያ ሞዴልና ዲዛይር ፣ በስብዕና የሴቶች ተቆርቃሪ ፤ የወጣቶች መካሪና ሀገር ወዳድ ናት ታዲያ ለዚህ ሁሉ መሰረት የሆናት ምንድን ነው?

ሳያት፡- (ትንሽ ሳቅ) ተፈጥሮዬን መቀበሌ ነው የሁለም ነገር መሰረት  የሆነኝ ብዬ ነው የማምነው። ለምሳሌ አንቺ የምትወጂውን ነገር ስታውቂና ስትቀበይ ለማሻሻልና ይበልጥ ለመስራት ትነሳሺ የለ? እኔም ፆታዬን ፣ ሰውነቴን ፣ መልኬን ፣ ተስዕጦዬና ተፈጥሮዬን አምኜ መቀበሌ ለሁሉም መሰረት ሆኖኛል።

ቅንድል፡- እሺ እስቲ ሳያት ወደ ኋላ ልመልስሽና ወደ ፊልሙ የገባሽበትን አጋጣሚ አስታውሽን ልፋት ነበረው ወይንስ አጋጣሚ ሆነ የተደላደለ መንገድ ጠበቀሽ?

ሳያት፡- እኔ አጋጣሚ ሆኖ ዕድለኛ ነበርኩኝ already ወ/ሪት ኢትዮጲያ አሸንፌ ስለነበር ቀላል ሆኖልኛል። እንደውም እኔ አልነበርኩም የምነጋገረው እንደዚህ መስራት እፈልጋለው ወይም እንደዚህ መስራት አልፈልግም የሚለውን ወ/ሪት ኢትዮጲያ ድንገት የመጣ ስለነበረ ቀጥሎ ለሚመጡ ነገሮች አልተዘጋጀውም ነበር። ወድድሩን ያዘጋጀው ድርጅት ፊልም ከሚሰሩ ድርጅቶች ጋር ተነጋግሮ ... ትዝ ይለኛል ዳሪክተሯ ሄሌን ትባላለች አሁን ከሀገር ውጪ ናት ት/ቤት በዕረፍት ሰዓት መጥታ አየችኝ ሃይስኩል ተማሪ ነበርኩኝ የዛኔ በሰዓቱ ለምን እንደነበረ አልገባኝም ነበር ከዚያ ከቀናት በኋላ እንደዚህ አይነት ስራ አለ ተዘጋጂ ተባልኩ። እንዲህ ነው ወደ ፊልሙ የገባሁበት አጋጣሚ።

ቅንድል፡- ሳያት በተለያዩ መድረኮች ስለ ስኬት ስትናገሪ ከትናንት ማንነታችን ፣ ከዛሬ እኛነታችን ጋር የምናደርገው የትግል ውጤት ነው ስትይ እናደምጣለን ነገር ግን ስኬት በንጽጽር ነው ብለውም የሚያምኑ አሉ ይህንን ሀሳብ ካንቺ የስኬት ትርጉም ጋር እንዴት ታይዋለሽ?

ሳያት፡- ሀሳቡ ትክክል ነው እኮ ስኬት በንጽጽር ነው አዎ ለዚያኛው ሰው ስኬትን በንጽጽር ለሚያስበው። ልክ እንደተሰጠን ህሊናችን ልክ ነው ስኬት ፈጣሪ ሲፈጥር ሁሉንም ልዩ አደረገንና ያንቺ የስኬት መጠን እና የእኔ አጠቃላይ ሀሳቡ መልካም ቢሆንም እኔ መልካም ነው ብዬ የማስበው ሌላ ነውአንቺም መልካም ብለሽ የምታስቢው ሌላ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ስኬት እንደግለሰቡ ነው። ሁሌም እኔ ነኝ ለስኬቴ ሚዛን ላወጣለት የምችለው። እንደዛ ባይሆን ኖሮ ልጅ እያለን ቤተሰቦቻችን ዶክተርሁኑ ብለው እንደመከሩን ዶክተር በመሆንን ነበር ወይም ስኬት ብዙ ብር በማግኘት ብቻ በተለካ ነበር። ግን እያደግሽ እየበሰልሽ ስትሄጂ ሕይወት ሲገባሽ አንቺም እየኖርሽ ሌሎችም እንዲኖሩ ስታደርጊ ስኬት ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ። እና እንዳልኩሽ እንደየ ሰው ነው የሚለያየው። አሁን እንደውም ሳናስበው ክፉ እንከን አውጪ እየሆንን የምንመጣው ሳንፈልግ እያነጻጸሩብን የእኛን ኑሮ፣ የእኛን ሀገር፣ የከፈልነውን መስዋዕትነት፣ ከራሳችን ጋር ያለንን ትግል በማያውቁ ሰዎች መሀል ንጽጽር ውስጥ እየገባን ነው እየከፋን የመጣነው።

ከጓደኞቻችን ጋር ተገናኝተንስቀን ፣ ኃዘቸውአሳዝኖን ፣ ደስታቸው አስደስቶን እንዳንመጣ የሆንነው መወዳደር እንዳለብን እየተነገረን ስላደግን ነው። So, ስኬት ንጽጽር መሆን አለበት ብዬ አላምንም እኔ በግሌ እና እንደ ሀሳብም ሰው ወስዶት ለማጤን ቢሞክር ትክክል ነው ብዬ አምናለው። አሁን ያለንበት የሀገራችን ሁኔታ እራሱ ከንጽጽር የመጣ ሆኖ እኮ ነው የተቸገርነው። ጎረቤትሽ ካለው፣ እዛኛው ሰፈር ካለው፣ እዛኛው ክልል ካለው፣ እየተባባልን ነው መንገዳችንን እየሳትን ያለነው። ለዚህ ነው ስኬት በንጽጽር ባይሆን ብዬ የማስበው ግን ስኬት በንጽጽር ነው ብለው የሚያምኑም ሰዎች ሌላ ሰው ላይ ጉዳት ሳያደርሱ ስኬታቸው ላይ መድረስ ከቻሉ ይሰራል ማለት ነው። ለኔ ግን ስኬት ከትናንትናው ማንነታችን ከዛሬ እኛነታችን ጋር የምናደርገው የትግል ውጤት ነው።

ቅንድል፡- እሺ ሳያት ከዚሁ ጋራ ላንሳውና ለሰዎች ስኬት መነሻው የህይወት መርህ ነውና አንቺን ለስኬት ያበቃሽ የህይወት መመሪያ ወይም ፍልስፍና ምንድነው?

ሳያት፡- ይህንን ነገር ብዙ ቦታ ብዬዋለው የሚገርምሽ የእኔ የሕይወት መርህ "መሸነፍን ያለመፍራት ወይንም ቅሌትን ያለመፍራት ነው" ቅሌት የምለው እኛ ሀገር "አሉ" እራሱ ስለሚከብድ ነው። አደርገዋለው ብለሽ አለማድረግሽ ግን ደግሞ ነገ እንደገና ተነስተሽ ለመሞከር የምትጥሪበት የአዕምሮ ብቃት ነው እና ሽንፈትን አልፈራም።

ቅንድል፡- እንግዲህ ብዙዎቻችን እኔን ጨምሮ ሳያትን ስናስብ ወደ አምዕሯችን የሚመጣው ነገር ወጣትነትን እና ዝነኝነትን በሚገባ አስማምታ በእውቅና የማይንገዳገድ ስብዕና ባለቤት መሆኗ ነው። እስቲ ወጣትነትሽን ከዝነኝነት ጋር ያስማማሽበትን መንገድ ብታካፍይን?

ሳያት፡- እኔ በምን አምናለው መሰለሽ የራሴ በጣም ብዙ እንደ ስህተት የሚታዩ በዕድሜ በአጋጣሚ፣ በሰው ተጽዕኖ ፣ ባለመገንዘብ የሰራዋቸው ብዙ የራሴ ስህተቶች አሉኝ። ለሰዎች ለመምከር የሚበቁ ነገሮች አሉ ብዬ አላስብም ግን ለእኔ ሰርቶልኝ የነበረበትን መንገድ መንገር እችላለሁ። ለምን መሰለሽ እኔ ባደኩበት መንገድ ያላደገና እኔ ባለፍኩበት መንገድ ያላለፈ አለ።

ለምሳሌ ልጅሽን ሌብነት ብቻ እያስተማርሽ አሳድገድገሽው አድጎ ሌባ ሲሆን ሌላ ሰው አይቶ ሲገምተው ስታይ ታዝኛለሽ ግን ልጁ የተማረውን ነው ያደረገው። እንደማህበረሰብ እኔ እና አንቺ እድለኛ ሆንና ተማርን ልበልሽ  እና ተምረን የአዕምሮ ስብዕና ብቃት የቱ ጋር ድረስ እንደሆነ አወቅን እንበልብቻ ሰዎች በዚህ መንገድ ቢሄዱ የህሊና እረፍት ያገኛሉ የምንለውም መንገድ አገኘን። ይህን ሳያውቁ ደግሞ ያደጉ አሉ። ሌላ መጥፎ መንገድን መከተል ጉብዝና የሚመስላቸው አሁን አሁን ነው ስበስል እየገባኝ የመጣው ነው የምልሽ "እንዴ እገሌ ለምን እንዲህ አደረገ? እንደዚህ ማድረግ ልክ ነው ወይ? እያልኩ አስብ ነበር። አሁን ግን ሳስበው ሰው ያወቀውን ነው የሚያደርገው ግን ከሁሉም የበለጠ ማለት የምፈልገው ሁሉም ሰው ወደ ህሊናው ሲቀርብ ትክክል እና መጥፎ የሆነው ይገባዋል፣ በአከባቢ ተጽዕኖ የሚያደርገውን ለይቶ ያውቀዋል። ፍኩኩር ያለመግባት አሁን እኔ ለምሳሌ እንደ ማንኛውም ሰው ከመካከለኛ ቤተሰብ የመጣው ነኝ። ግን እዛ ቤት ያለው ነገር እኛ ቤት ያለመኖሩ፣ በዕድሜ ፣ በመልክ፣ በሀብት ወይንም ሰዎች መድረስ አለብሽ ብለው የሚያስቡበት ቦታ ያለመድረሴ ችግር እንደሌለው አምኜ ስለምቀበል እራሴን አስታመምኩት ምክንያቱም መሸፈኛ አልፈለኩም አንዳንድ ጊዜ እንደውም የሆነ ቀን በጣም ሲከፋን ለብሰን እንወጣለን አይደል መከፋታችንን የሚሸፍንልን እየሰለን እና እነሱን ነገሮች ለማቆም ሞከርኩኝ በራሴ በምችለው አቅም ችግሬን የሚሸፍንልኝ እና ተጋፍጬ የማልፍበትን መንገድ መከተል ጀመርኩ። አለማወቄን ነው?.... እንዴት ነው ማወቅ የምችለው? ... አለማግኘቴን ነው? ... እንዴት ነው ማግኘት የምችለው? እነኚህን ጥያቄዎች እራሴን እየጠየኩ እና አራሴን እያጠነከርኩ ኖሬያለሁ ወደፊትም እኖራለሁ። እንዲህ እንዲህ እያልኩ ከራሴ ጋር ጊዜዬን ለማጥፋት ጥርሴን ነከስኩ። እሱ መሰለኝ በተወሰነ መንገድ በምንም አይነት ዝናም ሆነ ችግር የማይነገዳገድ ማንነት እንድይዝ ያደረገኝ። ጠንካራ የሆነ ማንነት ከበፊት ጀምሩ እየገነቡ መምጣት ከምንም ጋር እራስሽን አስማምተሽ እንድትኖሪ ይረዳሻል።

ቅንድል፡- እንደው ከዛው ሳንወጣ ለሳያት ወጣትነት እንዴት እና በምን ይገለጻል?

ሳያት፡- እኔ ወጣትነትን የምገልጠው በማይናወጥ ጽናት ነው። ወጣት የማይናወጥ ተስፋ እና ጽናት አለው። የሆነ ጠንከር ያለ ነገር የማይናወጥ መንፈስ አለው። ያመንሽበት ነገር መጥፎም ቢሆን ትሞቺለታለሽ። የወጣትነት ዕድሜ ለራስሽ፣ ለቤተሰብሽ ፣ ለአከባቢሽ ብሎም ለሀገርሽ አንድ አሻራ ጥለሽ ማለፍ የሚገባሽ ዕድሜሽ ነው። የብዙ ኃላፊነቶች ባለቤት ማለት ነው ወጣትነት ብናውቀውና ብንገነዘበው።

ቅንድል፡- በተለያዩ ሚዲያዎችና ቃለ መጠይቆች ሳያት በ ሴቶች ጤና እና እኩልነት ላይ እንደምትሰራ ሰምተናል ከዛም ባለፈ በተለያዩ ግዜያት ስለሴቶች ስትሟገት  አይተናል። እስቲ ሳያት የሴቶች መብት ፣ እኩልነት የሚረጋገጠው ሴቶችን ብቻ ለይቶ በማስተማር ፣ በማበረታት ነው ወይስ እንደ ማህበረሰብ ያለን እይታ ሲቀየር ነው? ይህን ጥያቄ ያነሳሁት በአንድ ወቅት ኢቢኤስ ቴሌቪዥን ላይ ቀርበሽ ስትናገሪ ብዙ ግዜ በሴቶች ዙሪያ ለስራ በምትሄጅባቸው ቦታዎች ሴቶችን ብቻ ሰብስበው እንደሚጠሩሽ አስታውሰሽ ችግራቸውን ለነሱ ደግሜ መናገር አልፈልግም ስትይ ስላደመጥኩ ነው።

ሳያት፡- ይሄ በጣም ሰፊ ሃሳብ ነው እንደዚህ ብለን የምንናገረው ነገር አይደለም። ምክንያቱም ያለነው ደሀ ሀገር ላይ ስለሆን። የመብላት፣ መጠለያ የማግኘት ፣ ጤና ጣቢያ ሄዶ ትክክለኛ ምርመራ የማግኘት እና የመታከም ችግር ላይ ያለን ሰዎች ነን። ትንሽ እንዲህ እናደርጋለን ብሎ መናገር ከባድ ነው። ግን መነሻውን ከአሁኑ ማድረግ እንችላለን። ሁል ጊዜ ቅር የሚለኝ ነገር ሴቶቻችን ይጠንክሩ ይበርቱ ብለን በተወሰነ መልኩ ከተማ ያሉ ሴቶችን እነቃን ግን ለነቁ ሴቶች የተዘጋጀ ማህበረሰብ የለንም። ሰርተን እንግባ ለሚሉና የእኔ ቢበልጥም አብረን ሰርተን መኖር እንችላለን የሚሉትን ሴቶች የሚቀበል ማህበረሰብ ሳናዘጋጅ የሴቶችን ወገን ብቻ ማጠንከሩ ምንም ይሄን ያህል ብለን የምናመጣው ለውጥ አይኖርም።

ሴቶች ተበደልን መብታችን ዕኩል አይደለም ካልን ከማን ጋር ነው የሆነው? ከዚያኛው ጾታ ጋር አይደል? ስለዚህ እንዲህ እኮ ቢደረግ እንዲህ ብናደርግ የሚለውን ከእነርሱ ጋር ነው መወያየት ያለብን። እኛ ነን ችግረኞቹ እርስ በእርስ ብናወራ እኛ ነን ተቸጋሪዎቹ እኛ እንዲህ ሆንን፣ መፍታችን አልተከበረልንም ብንል ሳናስበው ጽንፈኛ ነው የምንሆነው። ወደ መፍትሄ የሚወስዱንን ብዙ መንገዶች አናቀላቸውም። እንደ ማህበረሰብ ወንዶች ናቸው ማወቅ ያለባቸው። አሁን ለምሳሌ የቤተሰብ ምጣኔ ለሴቶች ብቻ ሲነገራቸው እኔ በጣም አዝናለው። ቤተሰብ የማፍራት የሴቶች ጉዳይ ብቻ አይደለም። ለምን ወንዶች በዚህ መልኩ ተጠርተው አይማሩም? ለምን አይነገራቸውም ? ስትይ "አይ ወንዶች ፍቃደኛ ስለማይሆኑ፤ ሴቶች በድብቅ እንዲያደርጉ ነው" ትባያለሽ ታዲያ እስከ መቼ አቋራጭ መንገድ እየሄደ ይዘለቃል? በአጠቃላይ ልክ አንቺ እንዳልሽውማህበረሰብ ላይ ነው በደንብ መሰራት ያለበት።

**ቅንድል፡-** ሌላው ለጥበቡ ቅርብ እንደመሆንሽ ከሴቶች ጋር ላነሳው የምፈልገው ጥያቄ ብዙ ግዜ የሀገራችንን የቴሌቭዥን ማስታወቂያ ስመለከት ሴቶች ዳይበር ሲቀይሩ እንጂ ሲገዙ አያሳዩም ፣ የልብስ ማጠቢያ ኦሞ ተገዝቶላቸው ሲያጥቡ እንጂ ሱፐር ማርኬት ሄደው ሲገዙ አያሳይም ሌላው ቢቀር ለ ባንክ ቤት የ ATM ማስታወቂያ አንድ ሴት ከፍቅረኛዋ ጋር ሆቴል ቁጭ ብላ እራት እየበሉ ሂሳብ መጦ ወንዱ የሚከፍለው ብር ሲያንሰው ወቶ ATM በመጠቀም ብር አውጥቶ ሲከፍል ያሳያሉ ይህ ሁሉ የሚሆነው ሴቷ አጠገቡ እያለች ነው። ታዲያ እነዚህ እና መሰል ማስታወቂያዎች የሴቶች የፋይናንስ ጥገኛነትን ከማሳየት በዘለለ ለእኩልነት የሰጡት ቦታ ያነሰ ነው እና ይህን አይነት ማስታወቂያዎችን እንደ ኪነ ጥበብ ባለሙያ ፣ እንደ ሴት ስትመለከቺው ምን አይነት ስሜት ይሰጥሻል? ለመለወጥስ ምን መደረግ አለበት ትያለሽ?

**ሳያት፡-** የሚገርምሽ ከዚህ ጋር በተቀራረበ አይነት ነገር ፊልም ላይ ተጠይቄ መልሻለው። አባትህ እንዳይሰማ ነው የሚባለው እናትህ እንዳትሰማ አይባልም ወይም ደግሞ ወንድምህ እንዳይቆጣ እንጂ እህትህ እንዳትቆታ አይባልም ወይ... ብዬ ጠይቃለሁ። ግን ሳስበው እኛው ነን የምንገልጸው ማህበረሰባችንን፤ ይሄን አውርቼዋለሁአንድ ቃለመጠይቄ ላይ እና እንደ ሴት በጣም ቅር ይለኛል። እንደ ሀገር ደግሞ በዚህ ባለው የፊልምም ሆነ ሀገራችን ውስጥ ባለው የጥበብ ኢንዱስትሪ ይበልጥ ሴቶች እንዲሳተፉ ከማድረግ አንጻር የሚደረገው ነገር አናሳ ስለሆነ የሚተላለፈው በወንድ ዐይን ነው። እና እነሱም የሚያዩት እንደዛ ነው። ግን በእነሱም አትፈርጂም ምክንያቱም የሚያዩትን እና የሚያደርጉትንጸነው። እኔ እና አንቺ የምናወራው የምናውቀውን ነው እና እነሱም የሚያውቁትን እና የሚያዩትን ነው የሰሩት። ስለዚህ ልክ ቅድም ከጠየቅሽኝ ጥያቄ ጋር ይሄዳል እንደ ማህበረሰብ ይህንን ካልነገርናቸው "ይሄ ነገር አንተም ልጅ ስትወልድ ሴት ልጅህ የምታየው ይህንን ነው ፤ መክፈል ያለበትም ወንድ ነው የማሏት" ብለን መነጋገር እስካልቻልን ድረስለውጥ አናመጣም።በነገራችን ላይ አቅልለው ያዩታል ብዬ አላስብም አንዳንዴ በተለይ ጥበብ ውስጥ ያለ ሰው ትንሽ ከማህበረሰቡ በአዕምሮም አስተያየት ትንሽ ሰፋ ባለ መንገድ ስለሚያዩ የጾታ ጽንፍ አለው ብዬ አላስብምምክንያቱም ጥበብ ውስጥ ስላለው አየዋለው። አለመገንዘብ ነው ይሄ የምንሰራው ሥራ ማን ላይ ጫና ይፈጥራል የምንልበትን ልክ እንደዚህ ያለ ፕላትፎርም አለመዘጋጀቱ እኮ ነው እንዲህ ያለ ስህተት የሚያሰራው። አሁን እንደጠየቅሽኝ ያሉ ጥያቄዎችን የሚጠይቅ እና እንዲህ አይነት ማስታወቂያ የሰሩ ባንኮችን የሚጠይቅ የለም። ፊት ለፊት ያስቀመጣቸው እዚያ ሁሉ ሴቶች እያሉ ተጠቃሚዎቹ ብዙ ሴቶች እንደሆኑ እያወቁ ለምን እንዲህ ትሰራላችሁ ብሎ ለመጠየቅም ሆነ ጫና ለማሳደር እንደማህበረሰብ ስላልሰራን ነው። ያልሰራሽውን ነገር ደግሞ ለምን እንዲህ ተሰራ... ለምን እንደዛ አልሆነም... ለማለት ይከብዳል። እንደዛ ከሚባል ደግሞ እኔ በማውቀው መልኩ ተጽዕኖ የሚፈጥር አይደለም ጥያቄ ሊፈጥሩ የሚችሉ ነገሮችን እያስተካከልኩ ነው የምሰራው። ይሄን ለማውቀው ሰው አስተላልፋለው። አንቺም ለምታውቂው ታስተላልፊያለሽ እንደዚህ እያልን እንስራ። ይህቺ እንኳ እኔ እና አንቺ የተወያየናት ነገር የሆነ ቦታ ሄዳ ለውጥ ታመጣለች ። እናንተ ባላችሁበት ስትቀጥሉ ሌላውም ሰው ባለበት መንገድ ሲገፋ ለውጥ እናመጣለን።



# "...ኢትዮጵያዊነት ለኔ ተስፋ ነው።..."

ቅንድል፡- ሴቶችና ወጣቶች ከ ሳያት የህይወት ትሩፋት ምን መማር አለባቸው ትያለሽ?

ሳያት ፡- እምምምም እኔ ቦታው ተገብቶኝ አይደለም ይሄን የምለው ግን ለሁሉም ሰው በተለይ ደግሞ ለሴቶች ማለት የምፈልገው ስህተትን አትፍሩ ነው። ስሩና ተሳሳቱ,,,,,,,,,,ውጡና ገንዘብ ባይኖራችሁም ንፁህ ልብስ ባትለብሱም መድረስ ያለባችሁ ቦታ ድረሱና ተመለሱ እንደው በይሉኝታ በጣም የታጠርን አይደለን? ቢሆንም ወጥተው ሰርተው ከተሳሳቱም ቢሳሳቱ ማንነታቸውን ፣ ክብራቸውን እና ሴትነታቸውን  የማይነካ ከሆነ መሳሳታቸውን አይፍሩ እላለሁ እኔ የማደርገው እሱን ስለሆነ,,,,, ሌላው ለወጣቶች የምለው ነገር እባካችሁ ሁሉምነገርበማስተዋል ይሁን ሁላችንም መሰዋት የከፈለልን ቤተሰብ አለን ይብዛም ይነስም ሁላችንንም የደረስንበት እንድንደርስ ቤተሰቦቻችን ለፍተዋል የኛን የሆነ ቦታ መድረስ በጉጉት የሚጠብቁ ቤተሰብ አሉን እንዲሁም ሃገር አለን ምንም ነገር ከማድረጋችን በፊት የመጣንበትን መንገድ የኛንም ሆነ የሌሎችን ቤተሰብ ማሰብ አለብን እና ሁሉም ሰው ወገን አለሁ ያም አንተ ነህ እሱም እኔ ነኝ እርስ በእርሳችን እንጎዳዳ የምናደርገውን ሁሉ በማስተዋል እናድርግ,,,,,,,,,,,ይሄን ነው ልል የምችለው።

ቅንድል፡- አስቲ ለሳያት ኢትዮጲያዊነት እዴት ይገለጻል? ሀገር ፍቅርስ እንዴት ይቃኛል?

ሳያት፡- ኢትዮጵያዊነት ለኔ ተስፋ ነው አለ አይደል ማን ያድርገው ማን ባናውቅም ፣ እንደዛ ይሁን እንደዚህ ባይገባንም ከሚመጣው ሁሉ በድል የምናሸንፍ አይነት ስሜት የሚሰማን? ሁላችንም ልብ ወስጥ ፍቅር አለ እውነተኛ ኢትዮጵያዊነት ያን ፍቀር ተመልክቱ በእኩል ሁሉንም መውደድ ማለት ነው። የሃገር ፍቅር ሲኖርህ ደግሞ በምንም ተዓምር ጎንህ ላለው ሰው ስጋት አትሆንም ተስፋው እንጂ ፤ ባህልሽን ማንነትሽን እንዲሁም ታሪክሽን ጠብቀሽ ትኖሪያለሽ ፤ የሃገር ፍቅር ሲገባሽ ለሃገሬ ምን አደረኩ ብለሽ እራስሽን መጠየቅ ትጀምሪያለሽ ,,,,,,እኔ እንዲህ ነው የሃገር ፍቅርን የምረዳሁ።

ቅንድል፡- ሳያት ደምሴን በፊልሞቿ ፣ በሙዚቃ ስራዎቿ እና በተለያዩ የማህበረሰብ ስራዎቹዋ ጠንከር ያሉ ሀሳቦችን ስታነሳ ይስተዋላል ከዚህ በተጨማሪ በስብዕና ልዕልናሽ ፣ በቃል አጠቃቀምሽ ፣ በአርያነትሽ ብዙዎች እኔን ጨምሮ የመጽሀፍ ስራ ቢኖራት እላለሁ እስቲ ስለ ግል ስኬትሽ፣ ትዝብትሽ እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ከሳያት መጽሀፍ መጠበቅ ይቻላል?

ሳያት፡- (ትንሽ ሳቅ) የሚገርምሽ ከአንቺ ጋር በዚህ ጉዳይ እስካወራንባቸው ቀን ድረስ ጭራሽ አስቤው አላውቅም ነበር እራሴን በመተቸት ጎበዝ ስለሆንኩ መሰለኝ የአዕምሮ ጥንካሬው ጋ አልደረስኩም ገና ነኝ ብዬ ስለማምን እንደዚህ መፃፍ እችላለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር አሁን ግን የእውነት በጣም አስብበታለሁ።

ቅንድል፡- እንደሚታወቀው ኮሮና የአለምን አኗኗር ቀይሮታል ታዲያ በዚህ ሳያት ግዜዋን እንዴት እያሳለፈች ነው?
ሳያት፡- እኔ ከኮሮና በፊትም ተመሳሳይ ህይወት ነው የነበረኝ በጣም ውስን ናቸው የኔ እንቅስቃሴዎች የምሄድበትና የማገኘው ሰው ውስን ነው ምክንያቱም የስራዬን መስመር ቀድሜ ስለዘረጋሁ አልከበደኝም። ግን ምን ተፅዕኖ አደረገብኝ መሰለሽሰው ማቀፍ አልቻልኩም። ሰው ማቀፍ ያለመቻሌ ትልቅ ትልቅ ተፅዕኖ አሳድሮብቻል። (ትንሽ ሳቅ) ሌላው ግዜዬን የማሳልፈው በማንበብ ነው አሁን አሁን ግዜዬን  ከአቅም በላይ በማንበብ አሳልፋለሁ።

ቅንድል፡- በቅርብ የለቀቅሽው እስክሽር የተሰኘ ነጠላ ዜማ በጣም ተወዳጅነትን አትርፏል ለዚህም ዋናው ምክንያት በሚል የሚነሳው መልዕክቱ ጥልቅ መሆኑና የተሰራው ምስል ስራውን ገላጭ ስለሆነ ነው። ከዚህ እስክሽር ከሚለው ትርጉም ጋር በተያያዘ በሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ወጣቶች እየሞቱ ነው ፣ ጥላቻ እየተሰበከ አንድነትና ፍቅር እየኮሰሰ ፣ እኛነት ጠፍቶ እኔነት ነግሶ ፣ ህጻናትና ሴቶች በሚያሳፍር መልኩ እየተደፈሩ ፣ ታላላቆች የማይከበሩበትና እምነትና ሀይማኖት የሚያስተምሩትን የሚፈራ እየተመናመነ እንደ ሀገር ታመናል። ታዲያ ከዚህ ሀገራዊ ህመም እንዴት መሻር እንችላለን ብለሽ ታምኛለሽ? እስክንሽር ድረስ ያለውን ህመም ለመቀነስና አዲስ ተስፋ ለማየት ከወጣቱ ትውልድ ፣ ከመሪዎች  ፣ ከኪነ-ጥበብ ሰዎች ፣ ከሀይማኖት አባቶች ምን ይጠበቃል ትያለሽ?

ሳያት፡- እምምም ይሄ በጣም ከባድ ጥያቄ ነው። እንደው ሁላችንም ይሄን ግዜ ይቅር በመባባል ብናልፈው ብዬ እመኛለሁ። በስተመጨረሻም ሁሉም ሰው ከመኖር ነውየሚማረው ያለፈ ታሪክ ስህተት መሆኑን የምናውቀው ሆኖም ከነበረ በንፅፅሩ የነበረም ነገር ሲጠፋ ወይኔ ይሄን መስራት ነበረብኝ የምትዪው ከመቆየት ነው። እና ሁሉም ሰው ማድረግ ያለበት ይቅር መባባል ነው ብዬ አስባለሁ። በቀኑ ፍፃሜ ማንም ሰው ዘሩን ፣ ብሄሩን ፣ ሀይማኖቱን ፣ የቤተሰቡን የኑሮ ደረጃ ፣ የቆዳውን ቀለምና ስጋውን መርጦ ወደዚህ ምድርየመጣየለም የተፃፈልን ነው። ወደዚህ ከመጣን በኋላ ብሄር ፣ ዘር ፣ ቀለም እያልን መከፋፈል ለመድን ግን እንደሰውኛ ስንፈጠር የተፈጠርነው አብረን እንድንኖር ነው።



እና ከህመማችን እንድንሽር ውስጣችን ያለውን ቁርሾ አውጥተን ጥለን ይቅር እንባባል ምንም ነገር ማጥፋት እኮ ቀላል ነው በውሃ ሁሉንም ነገር በአንድ ቀን ማጥፋት ይቻላል ግን ማልማት ፣ የጋራ የሆነ ነገርና የሚያመሳስለንን ነገር መፍጠር፣ ቀጣዩ ትውልድ የማያፍርበትን ታሪክ ለማቆየት ትዕግስት እና ይቅር መባባል ያስፈልገናል። የሃይማኖት አባቶችም የጥበብ ሰዎችም ሆነ መሪዎች በየቦታቸው ለህዝብና ለሃገር የሚጠቅመውን በማስተዋል ሲያደርጉ ልንሽር እንችላለን,,,,,,,,(ትንሽ ሳቅ)

ቅንድል፡- በመጨረሻ መጪው አዲስ አመት እንደመሆኑ እንደ ሰው በተስፋ ፣ በእምነትና በስኬት ከፍ ለማለት እናቅዳለን ስለዚህ ከሳያት በአዲሱ አመት ምን ስራዎች እንጠብቅ?

ሳያት፡- ይሄ ነገር ግን ሰርፕራይዝ ይሁንልኝ እባክሽ,,,,,,,,,, (ትንሽ ሳቅ)  እውነት ለመናገር እንዲህ ነው የምለው ነገር የለኝም ግን በሙዚቃው የመምጣት ሃሳብ አለኝ እእእእ በፊልሙም እንደዛው ሌላም ማስባቸው ነገሮች አሉኝ በጥቅሉ በቀጣዩ አመት የሆነ ስራ ይዤ እመጣለሁ። (ትንሽ ሳቅ)

ቅንድል፡- ሳያት ውድ ግዜሽን አክብረሽንና ፈቅደሽ ይህን ቃለ መጠይቅ ስላደረግን በቅንድል መጽሄት አንባቢያን ከመቀመጫዬ ብድግ ብዬ አመሰግናለሁ። መጪው ዘመን ለቤተሰብሽ ፍቅርን ፣ ለራስሽ ስኬትና መንፈሳዊ ከፍታን ፣ ለሀገራችንና ህዝባችን በተለይም ለአድናቂዎችሽ ፣ ለሴቶችና ወጣቶች እድሜና ጤና ሰጥቶሽ ብዙ ስራዎችን እንድትሰሪ የሚሆንበት እንዲሆን እየተመኘን መልካም በዓል ይሁንልሽ እንላለን።
ሳያት፡- አሜን አሜን አሜን! እኔም አመሰግናለሁ። እናንተም የተነሳችሁበት ሃሳብ በጣም ጥሩ ነው በርቱ ባስፈለኳቹ ሰዓት ጥሩኝ ከጎናችሁ ነኝ።

# የቅኖች ገፅ



## የአረጋውያን ምርኩዝ የሆነው ቅን አሳቢ

የሰው ልጆች በምድር ቆይታችን የተለያዩ ለሆኑ የምቾት ህይወቶች ተገዢ መሆናችን የማይካድ ሀቅ ነው። በተለይም በሀገራችን ኢትዮጲያ ያሉ ወጣቶችና ጎልማሶች በምዕራቡ አለም አማላይ የኑሮ ህይወት በመሳብ ለስደት መሄድ የተለመደ ከሆነ ሰንበትበት ብሏል። በዚህ ሁሉ መሀል ግን ከግላዊ ምቾት ከፍ ብለው ለወገኖቻቸው አለኝታ የሆኑ ጥቂት ግለሰቦች እንደ ሀገር የሚተርፍ መልካም ተግባራትን አጀብ በሚያስብል መልኩ ሲሰሩ ስናይ ያብዛልን ማለትም ተገቢ ነው። ሜቄዶንያ የአረጋውያንና የዐምዕሮ ህሙማን መርጃ መአከል በሀገራችን ከተቋቋሙ የበጎ አድራጎት ተቋም በተለይም ለሀገራቸው በጦር ሜዳ አካላቸውን ፣ በስራ አለም እውቀታቸውን ፣ ሀብታቸውን ለትውልድ ዛሬ ያዋሉ አረጋውያንን በመደገፍ ፣ በመንከባከብ እረገድ ቃዳሚውና ብዛት ያላቸው አረጋውያንን እና አዕምሮ ህሙማንን የሚንከባከብ ተቋም ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ታዲያ ይህ ተቋም እዚህ እንዲደርስ ብዙ ደጋግ ኢትዮጲያዊ ግለሰቦችና ተቋማት በተለያየ ግዜ  የራሳቸውን ድጋፍ ቢያደርጉም በተድላና በምቾት ከሚኖርበት የባህር ማዶ ህይወት ለዚህ መልካም ተግባር ተመርጦ በውርስ ያገኘውን ቤትና መኪና በመጠቀም ደጋፊና ጧሪ ያጡ አረጋውያንን ለመርዳት ይህንን መአከል ያቋቋመው ቢንያም በለጠ መመስገኑና የቅኖች ምሳሌ ተብሎ መወደሱ ቢያንስበት ነው ስትል ቅንድል ዲጂታል መጽሔት በአዲስ አመት ልዩ ዕትም ቅጽ2 ቁጥር 5 የቅኖች ገጽ ምሳሌ ስትል ልታመሰግነው ወዳለች።

ቢንያም በለጠ ሰው ለወርዳት ሰው መሆን በቂ ነው ብሎ ለብዙ አባቶችና እናቶች ጧሪ ለመሆን ከስጋዊ ምቾት የመንፈስ እርካታን ያስቀደመ ቅን ኢትዮጲያዊ ነው። ቅንነትና መልካምነት ብዙ በሚፈተንበት ምድር ከግለሰብ ከፍ ብሎ ለብዙዎች የሚሆን ትሩፋት መሆን መመረጥን ቢጠይቅም በመረጥነው መልካምነት ውስጥ ነውና ቅንነት የሚሰጠን ሁሌም ቢሆን የህይወት መንገዳች መልካነትን ያገዘፈ እንዲሆን ይህ ቅን አሳቢ ትልቅ ምሳሌ ነው። በሜቄዶንያ የአረጋውያንና የአዕምሮ ህሙማን መርጃ መአከል በአሁኑ ሰዓት ቁጥራቸው ከ 2000 በላይ የሆኑ ወገኖቻችንን በመንከባከብ ላይ ይገኛል። ቅንድል ዲጂታል መጽሄትም ይህንን ተቋም የመሰረተው ቢንያም በለጠን በቅኖች ስም እረጅም ዕድሜ ከጤና ጋር እየተመኘች የዚህ ዕትም የቅኖች ተመስጋኝ ስታደርግ በደስታ ነው። በመሆኑም መጪውን አዲስ አመት ስናከብር በየ አረጋውያን ማዕከሉ ፣ በቤተክርስቲያንና በመስጊድ ደጃፍ ያሉ ወጎቻችንን በመጠየቅና በመደገፍ በቅንነት እንድናሳልፍ ቅንድል አደራ ትላለች።

# የቅኖች ገፅ



## በሀገር ፍቅር የተለከፈው ተጓዥ ጋዜጠኛ

ባለፉት አመታት የጋዜጠኝነት ሙያ በስነምግባር ብቻ ሳይሆን በሀገር ፍቅርም በጉልህ የደመቀ የተከበረ ሙያ ነው። ይህ ሙያ የተነገረ ፣ የተሰራ ፣ የተቀበረን ታሪክ ፈልፍሎ በማውጣት ለህዝብ ማድረስና የገጽታ ግንባታ ላይ በመሳተፍ የሀገርን ገጽታ ከህዝብ አልፎ ለመላው አለም በማስተዋወቁ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው የማይካድ ሀቅ ነው። ይህ ሙያ በብዙ ፈተናዎች ታጅቦ ቢቀጥልም የሚጥሉ ፈተናዎችን እንደ መሸጋገሪያ ድልድይ እየተጠቀሙ ታሪከ እና እውነት የሚያቆዩ ግለሰቦች ጥቂት አይደሉም። ታዲያ ያ ግዜ በአዲስ የሙያው ባለቤቶችና ወጣት ጋዜጠኞች ተተክቶ መንገዳገድና ዝናን ለማግኘት ብቻ ተብሎ በእስፖንሰር መልካም ፍቃድ ላይ ተመስርተው መዝናኛ ብቻ በበዛው የ ጋዜጠኝነት ግዜ ላይ በጨለማ መሀል እንደ ፈካ ብርሀን ከእስፖንሰር ገቢ በላይ ለነገ ትውልድና ለስራው የሚጨነቀው ፣ እግሩ ለሀገሩ የማይደክመው ፣ አንደበቱ ከታሪክ ፤ ከሀይማኖት ማወድስ ፤ ከጥንት ስልጣኔ ማማ ላይ የማይወርደው ፣ ሙያን ከስነ ምግባር ፣ እውቀትን ከሀገር ፍቅር ፣ ሀገር ፍቅርን ከቃል በላይ በተግበር እየኖረ ፣ ከተነገረው በላይ የሀገሩን ስልጣኔ ከቦታው በመገነት መስክሮ ለሌሎች በማሳየት ሀገር እንድናውቅ ብቻም ሳይሆን በማወቅ ውስጥ እንድንወዳት አድርጎ በልዩ እይታ ከቴሌቪዥናችን መስኮት ዘወትር እሁድ 10 :00 ሠዓት ከተፍ የሚለው ተጓዡ ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩም ነው። ሄኖክ ስዮም በአሁኑ ሰዓት ለሀገራቸው እውነት ፣ ለሙያቸው ክብር ፣ ለህዝባቸው ፍቅር ከሚሰብኩ ጋዜጠኖች መካከል አንዱ ሲሆን የሀገሩ ሰው ነው። ሀገሩን የመውደድ ልክፍቱ ከሰሜን ተራራ እስከ ደቡብ ጥቅጥቅ ደን ከምስራቆች ደጃፍ እስከ ምዕራቡ የሀገራችን ክፍል ድረስ ሳይታክት እየተጓዘ ኢትዮጲያዊነትን አንብቦ ሳይሆን በሁሉም ህዝቦች ፍቅር በአይኑ አይቶ የሚመሰክር ሀገር ወዳድ ጋዜጠኛ ነው። እኛም ታዲያ እውቀቱን ለመልካምነት ፣ ለሀገሩ ሳይሰስት የሰጠ በመሆኑና ለሌሎች ወጣት የሀገራችን ጋዜጠኖች ምሳሌ ይናሆናል በሚል በቅንድል ዲጂታል መጽሄት በአዲስ አመት ልዩ ዕትም የቅኖች ገጽ ተመስጋኝ ስንል ላበረከተው እያመሰገንን በአዲሱ አመት ለሀገራችን ታላቅነት ከለፋው በላይ እጅግ የሚሰራበት እንዲሆን ዕድሜና ጤና እንመኛለን።

በርካታ ተቋማት የተለያዩ ድጋፎችን እና የቅንንነት ስራን እንደሚሰሩ እሙን ነው እኛም ከበርካቶች መካከል በየግዜው ወደ ቅንነት ተምሳሌት ማጀት እያመጣን ስለምሳሌነታቸው የምናመሰግን ይሆናል እስከዛው ቅኖችን ያብዛልን እንላለን።

# አዲስ አመት
# ሊመጣብህ ነው

አባት ዘመኑን ሙሉ ለፍቶ እርጅና ወደቀበት ። ካልጋው መነሳት በተሳነው ጊዜ የደረሰ ልጁን ጠርቶ ብዙ ቀን ታጉረው በረሃብ የሚጮሁትን ከብቶች ወደ መስክ እንዲያሰማራ ያዘዋል። ልጁ የታዘዘውን ለመፈፀም ቢሞክርም ፣ በጅራፍም ቢገርፋቸው ከብቶቹ ለመንቀሳቀስ ሳይችሉ ይቀራሉ። ልጅም ወደ አባቱ ተመልሶ የሆነውን አስረዳው። አባትም "ተመልሰህ ሄደህ ሁሉንም እግራቸወን ነካካላቸው። ከዚህ በፊት የታሰሩ እንዲመስላቸው ማታ ማታ እግራቸውን እንካካላቸው ነበር ፣እናም ያለ ምንም ገመድ እንደታሰሩ ሆነው ሳይራበሹ ያድሩ ነበር። " አለው። ልጅም የታዘዘውን ፈፀመ ፤ እግራቸው በተነካ ቅፅበት ሁሉም እየዘለሉ መውጣት ጀመሩ።

----------

አንዳንዴ ያሉ የማይመስሉን አእምሮአችን የሚፈጥራቸው ትብታቦች ወይም ከአካባቢ የተማርነው የረዳት አልባነት ስሜት(Learned–helplessness) ሁሌም በነበርንበት ቦታ አስረው ያቆዩናል። ለውጥና ስኬት ፣ እረፍትና እርካታ ተነስቶን ለገዛ ቅዠታችን እስረኛ (Self-im prisoned) ሆነን እንሰነብታለን።

አሁን ሰዓቱ ነው!!

ነገሮችን እንደገና የማሰብ የመሞከር የማምለጥ!
✔ስራህ ሰልችቶሀል?
✔ግብህ ርቋል?
✔ህልምህ አይፈታም?
✔ደስታ አልጠጋህ ብሏል?
✔መልካም አጋጣሚዎችህን ሁሉ ተጠቅመሃል
✔ ለዚህ ሁሉ ምክኒያት አለህ?
✔ምክኒያት ያልከው ነገር ትክክል ባይሆንስ ወይም ጭራሹኑ ባይኖርስ??
✔ ድክመትና ጥንካሬህን በሃቀኝነት ታምነህ ተዋውቀሃቸዋል?

ለዚህ ሁሉ ውጣ ውረድህ ፣ መታሰርህ ፣ አለመለወጥህ የሰጠኸውን ምክኒያት መለስ ብለህ ቃኘው። ለዚህ ይረዳ ዘንድ ራስህን የምትጋፈጥበት ቅፅ (Self Reflection tool) ከስር ይገኛል።
በርህን ዘግተህ ለራሰህ ታማኝ በመሆን ጥያቄዎቹን በዝርዝር መልስ ። በመልሶችህ ውስጥ ራስህን በማየት በራስህ ለመታረም ትጋ። መጀመሪያ ከልብህ ለራስህ ሙሉ ይቅርታ ስጠው። ሌላው ከዚህ በኃላ ይደርሳል። ይሄን ሳታደርግ ቢያንስ ቀጣዩ አዲስ ዓመት አይጥባብህ!

©ሱራፌል አየለ

**ነዋል አቡበከር**
በመቀሌ ዩኒቨርስቲ የጋዜጠኝነት እና የኮሚኒኬሽን መምህር
newalabubeker13@gmail.com



# ምኞት ያሰከረው የሰው ልጆች የዘመን መለወጫ

ዘመን ከዘመን ሲለወጥ ፤ የዘመን መቁጠሪያዎችቻችን ወደፊት ሲራመዱ ፤ አዲስ አመት ሲጠባ ፤ አደይ ሲፈነዳ ፤ ምድርን ተስፋ ሲሞላት እኛም "እሰይ አዲስ አመት እንቁጣጣሽ እንኳን ደህና መጣሽልን" ብለን መቀበል፤ ከመፈቃቀሩም ከመጠያየቅ መዘያየሩንም ሁሉ ያውቅበታል ሀበሻ።

ታዲያ ከነዚህ ጋር ሁሉ አብሮ የሚሄደው ጥልቅ የመለካም ዕድል ምኞት መብዛት አስገረመኝና ለመሆኑ ሌላው አለምስ አዲስ አመትን እንዴት ያከብር ይሆን ስል የ Google ን ቋት በረበርኩኝ።ያገኘኋቸው መረጃዎች ግን አጃኢብ የሚያሰኙ ሆነው አገኘዋችው። ለካስ ባለፉት ነገሮች የተማረረው የሰው ልጅ በአዲሱ አመት መልካም እድል እንዲገጥመው የማያደርገው ድርጊት ፤ የማይከውነው ነገር የለም።

የምተርክላቹ በእንግዳ ባህልና ልምዳቸው አለምን ስለሚያስገርሙት የኬንያ አርብቶ አደሮች ወይም የሀመር ሰዎች አልያም የአማዞን የጫቃ ነዋሪዎች አይደለም። የማወራቹ  አጉል ልምድና ባህልን ፤ ምክንያት አልባ  ድርጊትና እምነትን አልፈናል ስለሚሉትና ስለሚንቁት የምዕራባውያን ሀገራት አዲስ አመታቸውን መልካም ለማድረግ የሚከውኑት አሰገራሚ አንዳንዴም አስቂኝ ልምድ ነው።

ለምን ከአየር ላንድ አንጀምርም።  እንደው አንዳንድ ግዜ ህይወት ምርርር አድርጋቹ ፤ መኖር አንገሽግሿቹ "ኧረ የት ሂጄ ኡኡኡ ልበል?" ብላቹ አታውቁም? "እንደው መንግስት ግን ምን አለ የመረረው ሁሉ እየሄደ "ኡኡኡ" ብሎ ያለ ሀፍረት የሚተነፍሱበት ተቋም ቢያቋቁም።አሁን እንባን ከመጠበቅ ይሄ አይቀልም?" ብለው ተመኝተው አያውቁም? የኛ ይቆየን። አየርላንዳውያን ግን ለዚህ ፍቱን መፍትሄ አዘጋጅተዋል።  በእነሱ የአዲስ አመት ወቅት የተለመደ አንድ ልምድ አለ። ዳቦ ደጃፋቸው ላይ ማንጠልጠል።"መጥፎ መንፈስን አሽቀንጥሮ የበዛ ፀጋን ይስባል "ብለው ያምናሉ። ታዲያ የዳቦው መጥፍ መንፈስን የማስወጣት ስራ የሚሰራው እስከ ደጃፍ ድረስ ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ ፍፁም እንዲጠፋ የሚከወን አንድ ድርጊት አለ። ከቤት የወጣው ክፉ መንፈስ ፈቀቅ ብሎ ከደጃፍ እንዳይጠብቃቸው በእኩለ ለሊት ድቅድቅ ጨለማ ወደ በራፋቸው ይወጡና "ኡኡኡኡኡኡ" ብለው በጩኸት ያቀልጡታል። ህፃን አዋቂው፤አዛውንት ወጣቱ የሚችለውን ያህል ሁሉ ይጮሀል። በጩኸቱ የድሮውን አባሮ "አዲስ አመት ሆይ በል አሁን ግባ" ሊሉ። ደግሞ ይኼኛው አርጅቶ ጮኸው እንዳስገቡት ጮኸው እስኪያወጡት።

#አጃኢብ

አስተውሉ እንግዲ አየርላንዳዊያን አዲስ ዘመንን አስታከው አገር ምድሩን በጩኸት ሲያቀልጡት የዴንማርክ ሰዎች ደግሞ አዲስ አመትና የቤት እቃ መስበር የኛ እንቁጣጣሽና አበባይሆሽ እንደማለት ነው። አይነጣጠሉም።ልክ የኛ ታዳጊዎች አዲስ አመት ሲደርስ ስዕል ስለው አልያው ካርድ አዘጋጅተው ስጦታ እንደሚሰጡት ዴንማርካውያንም በአዲስ አመት የፍቅር መግለጫ ድርጊታቸው የቤት እቃዎቻቸውን አውጥተው የወዳጆቻቸው ቤት ላይ እንደ ናዳ መሰባበር ነው።ብርጭቆ አይቀር ሸክላ ፤ ማንኪያ አይቀር ሹኪያ ከማዕድ ቤት እየተጓዘ ሊያውም በእኩለ ለሊት ይወረወራል ይሰበራል። "ታዲያ የሚወረወርበት ሰው ምንም አይልም?"ብለው ግራ እንዳዳይገባዎት።

የዴን ማርክ አባወራ የወዳጆቹን ብዛትና የፍቅራቸውን መጠን የሚለካው ከደጃፉ በተከመሩ የእቃ ስብርባሪዎች ነው። ለሊቱ በብርጭቆ ስባሪ ካልተናወጠ ፤ጣሪያው ካልተንጋጋ አውዳመቱ አይደምቅም አይሞቅም።
መቼም በበዐል ወዳጅ ዘመድን መጠየቅ የበዐሉ ድምቀት መሆኑ ጥርጥር የለውም።"ተሰብስበው ካልበሉ፣ ካልተጓረረሱ፣ ካልተገባበዙ ምኑን በዐል ሆነ " ይሉ የለ ደጋግ እናቶቻችን። ነገር ግን በዐሉ የሚከበረው ከሙታን ጋር ወይም ከእንሳስ ጋር ሲሆንስ? አዎ ቺሊያውያን የዘመን መለወጫን የሚያከብሩት ከሙታን ወገኖቻቸው ጓን እያወጉና እየተጫዋወቱ ነው። ሮማንያን በበኩላቸው አዲስ አመት የቤት እንስሳዎቻቸውን ማዕድ ጋብዘው በቋንቋቸው ሊያወጓቸው እየጣሩ በአሉን በደስታ ያሳልፋሉ። በበሬውን ወይም በጉን ፣፤ ዶሮውን አልያም ፈረሱን ከመዐዱ ጋብዘው "ብሉ በሞቴ... ያዙ እንጂ... ከምን ልጨምር" እየተባባሉ መሆኑ ነው። ለምን ቢባል? መልካም እድልን ፍለጋ ነው። ይህ ድርጊት መልካም ፀጋን እንደሚያመጣ ስለሚያምኑ።

የመልካም ነገር ናፍቆት ሪስያውያንም ብዙ ያደርጋል። በሩስያ የአዲስ አመት ዋዜማ የሚከወን አንድ የታወቀ ልማድ አለ። ታዲያ ችቦ ማንደድ አይደለም። እንዲህ ነው ነገሩ። የአዲስ አመት ዋዜማ ምሽት ላይ ሩሲያውያን በያሉበት ሆነው በቀጣዩ አመት እንዲሆንላቸው የሚፈልጉትን ነገር በወረቀት ይዘረዝራሉ። ዘርዝረውም አያበቁም ያቃጥሉታል። ማቃጠላቸውም አይደለም አስገራሚው ነገር። አመዱን ሰብስቦ በማንሳት ከውስኪ ጋር ቀላቅለው ግጥም አድርገው መጠጣታቸው እንጂ።

ያለፈውን መጥፎ ትዝታ ፍቆ መጪውን ብሩህ ያደርገወ ዘንድ የሰው ልጆች የሁሉም ግዜ ተስፋ ነው። አዲስ አመት ሲመጣ ደግሞ ይህ ስሜት ገዝፎ ልምድና ባህልን ወለደ። ይህም ብዙ አስደናቂ እምነቶችን እንዲፈጥር አደረገው። እናም ምኞት ያሰከረው የሰው ልጆች የአዲስ አመት አከባበር እንዲህ ባሉ አጃኢበተኛ ድርጊቶች የታጀበ ሆኗል ነው የዚህ እትም የአጃኢብ አምዳችን ተረኩ።
ታዲያ እንደ ኢትዮጵያዊ ቀጣዩ አመት መልካም ይሆን ዘንድ እሪሪ ብሎ መጮህ ወይም እቃ መስበር አልያም አመድ በውስኪ መጨለጥ አያስፈልገንም።ከየፈጥሮ ጋር የተናበበ በውበትና ስነ ስርዐት ያማረ ውብና የሚያኮራ የመልካም ምኞት መግለጫ ባህል አለን። ምርቃቱ ቄጤማው አበባውና ፀሎቱ ሁሉ! ይህን ጠብቆ ማቆየት ይገባናል።
እንባቢያን ሆይ አዲሱ አመት ከመመኘት ወደ ማግኘት የምንለወጥበት፤ እንደ አደይ ህልማችን የሚፈካበት፤ እንደሳሩ ተስፋችን የሚለመልምበት ፤እንደ መሬቱ አረሙ ከስሞ ፍሬው የሚያብብበት ይሁንልን። ስደተኛው ለቤቱ ቤተኛውን ለክብር ያብቃልን። ፍቅራችንን መከባበር ፤ መከባበራችን መተላለፍን ይውለድልን። በቅንነታችን በበጓነታችን እና ለሀገር ወዳድነታችን የሚሆን ሰፊ ልቦና ያለምልምልን።
ሰናይ አዲስ ዘመን!

#አዕምሮ ጤና




**ፊራኦል መስፍን**
በመቀሌ ዩኒቨርስቲ የአዕምሮ ሀኪም እና መምህር
firaolmesfin8@gmail.com


# የአዲስአመት እቅድ ስነልቦና

በአማካይ 50% የሚሆነው የህብረተሰብ ክፍል በአዲስ ዓመት አዲስ እቅድና ውሳኔ ያለው ሲሆን 10% የሚሆነው ብቻ ከእቅዱ ጋር ለጥቂት ወራት አብሮ እንደሚቆይ ጥናቶች ያመለክታሉ። አዲስ እቅድና ውሳኔ ሰዎች አዲስ ዓመትን በተሻለ ተነሳሽነትና ተስፋ ለመጀመር የሚረዳ ቢሆንም በእቅድ መሰረት መጓዝ አለመቻል እና አለማሳካት በራሱ ለከፍተኛ ጭንቀትና ተስፋ መቁረጥ ሊያጋልጥ ይችላል።

በአብዛኛው ጊዜ ሰዎች ለአዲስ ዓመት ክብደት መቀነስ፣ ከሱስ መላቀቅ፣ የተስተካከለ አመጋገብ ስርዓት መከተል፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መጀመር፣ አዲስ ስራ መፍጠርና ቁጠባ መጀመር በዋናነት ከሚጠቁሱት እቅዶች ውስጥ ናቸው።

የአዲስ ዓመት እቅድና ውሳኔ ከማይሳካበት ምክንያቶች በጥቂቱ ፡-

እጅግ የበዛና የተለጠጠ እቅድ፣ በተቀመጠው ጊዜ ሊሳካ የማይችል እቅድ፣ ያለንን አቅም ያላገናዘበ እቅድ ማቀድ ዋነኞቹ ናቸው ። ያልተጋነነ፣ ሊሳካ የሚችል እቅድ ማቀድ ዓመቱን ሙሉ ከእቅዳችን ጋር አብረን እንድንቆይ እና በስኬት እንድንራመድ እንደሚረዳን ይታመናል።

## ጥሩ እቅድ ለማቀድ ጠቃሚ ምክሮች

**1 በትንሹ መጀመር፡-**

ብዙ ነገር ለማከናወን በትልቁ የሚጀምሩ ሰዎች ብዙ ጊዜ ከብዙ እቅዶቻቸው መሃል አንዱንም ሳያከናውኑ በዋዛ ፈዛዛ ቀጣዩንም ዓመት ያሳልፉታል ። እንደውም ምሁራን እንደሚሉት ሦስት እና አራት እቅድ ያቀዱ ሰዎች ከአንድ እስከ ሁለት እቅድ ካላቸው ጋር ሲነፃፀር ያነሰ ስኬት ይኖራቸዋል ። ይባስ ብሎ ደግሞ ከ አራት በላይ አቅድ ያላቸዉ ደግሞ ከአንዱንም ሳይሆን ያለ ስኬት ዓመቱን ያሳልፉታል ። በትንሹ መጀመር ለረጅም ጊዜ ውሳኔያችንን ጠብቀን እንድንጓዝ ይረዳናል ። ትናንሽ እርምጃዎች ወደ ስኬት ይመሩናል ።

## 2 ራስን በጊዜ አለመገደብ :-

ከላይ የተጠቀሱትን ለማሳካት የግድ አዲስ ዓመት መጠበቅ የለበትም፤ በየትኛውም አጋጣሚ እነዚህን ውሳኔዎች መወሰንና ለተግባራዊነቱ መስራት ያስፈልጋል ። የጊዜን ገደብ ማበጀት የእቅዳችንን  መሳካት ወይም አለመሳካት ለመፈተሽ የሚያግዝ ቢሆንም በህይወታችን ውስጥ ለውጥን ለማምጣት እና ስኬታማ ለመሆን አዲስ ዓመትን መጠበቁ ተገቢ አይደለም ። እያንዳንዱን ጊዜ በመዋጀት ያገኘነዉን አጋጣሚ በሙሉ አሟጠን መጠቀም ስኬታማ ያደርገናል ።

## 3 በአንድ ጊዜ አንድ ተግባር ላይ ብቻ ማተኮር :-

ያልተገባ ባህሪይ የሚመጣው በጊዜ ሂደት ነው ። በመሆኑም በተስተካከለና በአዎንታዊ ልማድ ለመተካት ጊዜ ያስፈልጋል ። ለምሳሌ ከ አደንዛዥ ዕፅ ሱስ ለመላቀቅ ወይም አካላዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ክብደትን ለመቀነስ አቅደን ስንነሳ በአንድ ጊዜ የሚሳካልን ይመስለናል ። እውነታዉ ግን ለውጥ ሂደት እንጂ በአንድ ጊዜ ሮጠን የምንጨርሰዉ ሩጫ አይደለም ። እድሜ ልካችንን አብሮን የሚቀጥል ነገር እንጂ።

## 4 ስለ እቅዳችን ማውራት:-

የየዕለት እንቅስቃሴያችን ለቅርብ ዘመድ ወይም ጓደኛ ማውራት እንዲሁም ተመሳሳይ ፍላጎት ካላቸው ሰዎች ጋር መተባበር በእቅዳችን እንዳንሰላችና ወደ ስኬት እንድንጓዝ ይረዳናል ።

## 5 እገዛ መጠየቅ:-

በእቅዳችን መሰረት እየተጓዝንና እያተሳካልን ካልሆነ ከፍተኛ ጭንቀት እንዲሁም ተስፋ መቁረጥ ውስጥ መግባት ሊከተል ይችላል። በመሆኑም እገዛ መጠየቅ እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን የእእምሮ ህክምና ባለሙያ ወይም የስነ ልቦና ባለሙያ ማማከር ያስፈልጋል፡ በአዲስ ዓመት አዲስ ውሳኔና እቅድ ያላቸው ሰዎች እቅድ ከሌላቸው ሰዎች በአስር እጥፍ የተሻለ ህይወታቸውን በስኬት የመምራት እድል እንዳላቸው የአሜሪካ የስነ ልቦና ባለሙያዎች ማህበር ጽፏል ።
መጪው ዘመናችን ያቀድነውን የምናሳካበት መልካም ዓመት ይሁንልን !

ምንጭ:- Psychology Today & PsychCenteral







የቅንድል ኢትዮጲያ ባለራዕይ ወጣቶች ማህበር ቤተሰቦች አዲሱን አመት ምክንያት በማድረግ በደብረብርሃን እና በኮቸሬ (ጨለለቅቱ) ለሚገኙ አቅመ ደካሞች የበዓል ጥየቃ አከናውነዋል።

አዲሱ ዓመት የተቸገሩትን የምናስብበት ፣ የምንተጋገዝበት ፣ በአብሮነት ለመስራት እና ለማደግ የምንነሳበት ይሁን። 2013 በቅንነት ችግርን ፣ መለያየትን ፣ ጥላቻን ፣ ክፋትን ድል የምናደርግበት እና በአበሮነት ወደ ከፍታ የምንወጣበት የድል ዓመታችን ነው!

ቅን ፣ ምክንያታዊና ሀገር ወዳድ ትውልድ ለኢትዮጵያ!


# ምርትና አገልግልሎትዎን በቅንድል መፅሔት ያስተዋውቁ!

ለበለጠ መረጃ
(+251- 912178520
(+251- 920019699

#ይመለሱ ይሸለሙ



# ይመለሱ! ይሸለሙ!

ውድ የቅንድል ዲጂታል መፅሔት ቤተሰቦች በባለፈው ቅፅ 2 ቁጥር 4 እትማችን በሁለት ዘርፎች ማለትም በስነ-ፅሁፍ እና በፎቶግራፍ ዘርፍ አሸላሚ ውድድር ማዘጋጀታችን ይታወሳል። በውድድሩ እጅግ ብዙ ሰዎች ተሳትፈዋል። በውድድሩ የተላኩልን አብዛኛዎቹ ፅሁፎች አስተማሪ ቢሆኑም በዳኞች ውሳኔ አሸናፊ የሆኑትን አምስት ፅሁፎች እና አንድ ፎቶግራፍ ወደ እናን እናቀርባለን። አሸናፊዎች የዶ/ር ኤሊያስ ገብሩ ስራ የሆነውን ቢያ ተኮ/አንድ ሀገር የተሰኘውን መፅሐፍ ተሸላሚ ይሆናሉ።

የት ነህ !?
የት ነዉ ያንተ ግርዶሽ ?
የት ነዉ ያንተ ጉሬ ?
የት ነዉ ያንተ ሰብል ?
የት ነዉ ያንተ ፍሬ ?
በከንቱ ገለባ ስትሞላ አገሬ ።
እሳት ሲነድባት
ቋያ ሲወርድባት
ስትቃጠል ህልምህ
ስታምድ አገርህ
የት ነህ ?
አንተ የት ነህ ?
ከማን ጋራ ቁመህ ?
ሞቷን ካልሞትክላት
ጣሯን ካልጣርክላት
ሰዉ አይደለች ሀገር ፥ አልቅሰህ
አትቀብራት ።
✍ ቴዲ ካሳ

አራት ጣት
"ከአምስቱ አራት ብቻ
ቤቱ ጨሰ በጥላቻ"
የልጅ የማይመስል የማያጫውት፣
ዙሪያን አስተውሎ
ከልብ ኮሮጆ ሀዘን የሚከት
"እንቆቅልሽ?" ስትል
"ምን አውቅልህ" ብዬ
ግራ ጥያቄህን በቀኝ ተቀብዬ
'ካምሮዬ ጥጋት - መልስ አሰላስዬ
አልፈታ ቢለኝ ውስብስብ ሃሣብህ
"ሃገር ስጪኝ" ስትል፦
በቀና ልቦና - ሀገሬን ሰጠሁህ
አንተም መልሴን ትተህ፣
ሃገሬን ቀምተህ ፣
የሄድህ ይመስለኛል፣
ከጨዋታው ወዲህ ሃገር ጠፍቶብኛል ፤
እግሬ የቆመበት የምኖርበቱ፡
ያልተወለድኩበት ባዳ ሆኖብኛል።

አልወሰድካትም? አጥተሃታል?
ጠፍታሃለች አንተንም???
ዋሽተህ እንደሁ
በተረትም በታሪክም - ከመወቀስ
አትድንም።

ናላህ ዞሯል?
ሰልችቶሃል?
መጠራረብ መች ይበጃል
ከህብረትህ ጎን - ባዶነት ሲነግስ
ካንድነት ጣራ -ከፍቅር ጎራ
ምንም ሲፀነስ
አስር ትሆናለህ ሀያ ሰላሳ
መዋደድ ከስሞ ጥል ድል ከነሳ።
ተማረሃል ልክ እንደእኔ??
ኮስምነሃል በፍቅር ጠኔ??
ከወንድምህ 'ሰው'ነት ላይ
እጅህን ለክፉ አታንሳው
ምን ይመስልሃል ዋርካን
ከከፍታ የሚያወርደው?
ከብረቱ ስለት
ከአፈላለጥ ብልሃት
ከቆራጩ ጉልበት
ተዋጥቶ አይደለም ዛፉ የወደቀ
የመጥረቢያ እጀታ እንጨት መሆኑ ነው
ዋርካ ሚያስጎነብስ ልብ እያስጨነቀ።
ወንድም እያነቀ።
አጓጉቶሃል የጥል ማብቂያ?
ናፍቃሃለች ኢትዮጵያ?
ከፍ አርግ እጅህን ተመልከት
ይቅር የምንልበት
ፍቅር የምንሆንበት
ጠፍቶብናል የማርያም ጣት።

# እኔ...የእኔን

"ከአምስቱ አራት ብቻ
ቤቱ ጨሰ በጥላቻ"
የልጅ የማይመስል የማያጫውት
ዙሪያን አስተውሎ
ከልብ ኮሮጆ ሃዘን የሚከት
የእንቆቅልሽህ ዙሪያ ገብ እውነት
የጥያቄው መልስ ነበር "አራት
ጣት"።
✍ ሐና አበበ
(አዲስ አበባ)

እያንዳንዱ ሰው የሁለት መልክ ባለቤት ነው።የውጭ መልክ እና የውስጠኛው ማንነት። አንድ ሰው ሌላን ሰው ሲያይ የመጀመሪያ የሚያየው የውጪን ገጽታ ነው። ይህ የፍላጎት ሳይሆን የተፈጥሮ ግዴታ ነው። አይናችን ከላይ ከላይ ከሚታየው ገፅታችን ተሻግሮ ልቦናችንን የመመልከት አቅም የለውም።ለዚህም ይመስላል ብዙዎቻችን ከላይ ለሚታየው መልካችን አብዝተን መጨነቃችን፤ እርግጥ ነው ማማርን መውደዳችን ግን የሰው ልጅ በሰው ከሚዳኘው በላይ በፈጠረው ጌታ ይዳኛል፤ የሃያሉ ጌታ ዳኝነት ደግሞ ከማንም ድብቅ በሆነው እና ለሱ ግልፅ በሆነው ማንነታችን ነው ።ለዚህም ነው ለውጫዊ ገፅታችን ከምንጨነቀው በላይ ለውስጣዊ ማንነታችን መጠበብ ያለብን።

መኖሪያ ቤታችንን የምናፅዳው ከውጭ ለሚመጣው እንግዳ ሳይሆን ከውስጥ ለምንኖርበት ለእኛው ብለን መሆን አለበት። ም/ያቱም ከውጭ ለሚመጣው እንግዳ ብለን ያፀዳን እንደሆነ እንግዳችን የቀረ ሰሞን መኖሪያችን የቆሻሻ መነሃሪያ አለፍ ሲልም የሸረሪት ድር መኖሪያ መሆኑ አይቀርም። ለራሳችን ብለን ያፅዳነው ቤት ከውጭ ለሚመጣው እንግዳም መልካም እይታ ብቻ ሳይሆን ቆንጆ ማረፊያ መሆኑ እርግጥ ነው።

የሰው ልጅ ልክ እንደሚኖርበት ቤት ሁሉ ልቦናውን ሚያፅዳው በዙሪያው ላሉ ሰዎች ሳይሆን ሁሌም በፍርድ ላይ ስለሚሆነው ህሊናው መሆን አለበት ።ሰው አያየንም ብለን በልባችን የምናኖራቸው መጥፎ ባህሪያት ውሎ አድሮ እንዳልተፅዳው ቤት አቧራ መሆኑ አይቀርም ።በልባችን የኖረ ቂም በቀል ክፋት ራስወዳድነት እና ጥላቻ ልክ እንደ ሸረሪት ድር ዙሪያችን ከቦ ውስጣችንንም ወጪያችንንም ማጠልሸቱ አይቀርም።በአንፃሩ ደግሞ በመልካምነት በፍቅር በሰላም እና መሰል መልካም ባህሪያት የተሞላች ልብ ከራሷ አልፋ ለፊት ፈገግታ ለህሊና እረፍት መስጠቷ ሀቅ ነው ። ለልብ እረፍት ,ለህሊና እርካታን የሚሰጥ ስብእናን ከመገንባት የተሻለ ስኬት የለምና በአይናችን የምናየውምንም የማናያውምንም አቧራችንን ከስብእናችን ላይ ማራገፍ በይደር ማይቆይ ተግባር መሆን አለበት። ሀገር የተለያዩ ማህበረሰቦች ድምር ውጤት ናት። ማህበረሰብ ደግሞ የተለያዩ ቤተሰቦች ስብስብ ነው።ቤተሰብ ደግሞ በተለያዩ ግለሰቦች የሚገነባ ተቋም ነው። ስለዚህ የግለሰብ ስብእና መቃናት ትርፍ እናት ሀገርን እስከማቃናት የገዘፈ ነው። ለሀገራችን በጎ ለማድረግ ለጦርነት መዝመት ወይም የመንግስት ባለስልጣን መሆን የግድ አይልም። በእለት ተእለት የህይወት መንገዳችን ለምናገኛቸው የሀገር ልጆች ቀና ቀናውን በመመኘት በጎ በጎውን በማድረግ ሀገርን መጥቀም ይቻላል። ምንም እንኳ ኢትዮጲያ ከ100ሚሊዮን በላይ ልጆች ቢኖርዋትም ለእናት ሁሉም ልጅ እኩል ነውና የሁላችንም ወንድማማችነት እህታማማችነት ጥያቄ ውስጥ መግባት የለበትም። ሰፊ ያውም በተፈጥሮ ገፀበረከቶች የታደለች እናት ልጆች ነንና ጥቃቅን አጀንዳዎች ሊያሳንሱን አይገባም።ልባችንን በመልካምነት እና ቅንነት እናክም። ለእራሳችን፣ ለቤተሰባችን እና የህይወት መንገድ ለሚያገናኘን ለሁሉም ቀና እንሁን።እኔ የእኔን አንተ የአንተን አንቺም የራስሽን ሁላችንም የየራሳችንን መንገድ የሰላም እናድርግ ያኔ እናት ሀገሬ እናት ሀገራችን ሰላም ትሆናለች። ሰላም!
✍ሀናን ሳብር (አዳማ)

# #ይመልሱ ይሸለሙ

ከዘራፊዉ ማስታዎሻ

መቸም የዘራፊ የዘመን ምህዋሩ ከሰዉ ጫንቃ ሆኖ:
ማን መጉዋዝን ይሻል ከፈራረሰ ቤት ሲሳይን ተማምኖ?
ለሞትም ይበሉት ለዘላልም ጸጸት ለዘመናት ገድል:
የሰዉ ልብ ይሞላል የኪሱ ሲጎድል:
ሁሌ እንደሚባለዉ:
የትንቢቱ ዳራ ተፈጽሟል ይሄዉ::

እኩለ ሌሊት ነዉ;
በሰማይ ምጣድ ላይ እርቃነ ጎድሎ ጨረቃ ተንጋላ:
አንዱን ልትገድል አንዱን ልታበላ:
አንድ የቤት ዘራፊ እያጉተመተመ:
በለስ ስላልቀናዉ እየተራገመ:
ማንም ከሌለበት አጥሩ ከዘመመ:
መኖሪያ ቤት ደርሶ:
የእድሉን ሊሞክር ገባ አጥሩን ደርምሶ:
በሩን አፈራርሶ:
ወለል መሀል ቆሞ ግራ ቀኝ ሲያማትር:
ምንም ዳና የለም ካንድ ከራሱና ከቤቱ በስተቀር:
ትንንሽ አይኖቹን ወደ ጣሪያዉ ላከ:
ግድግዳዉ መሀል ላይ የተንጠለጠለ:
ራሱን በትቢያ በድር የጠለለ:
አሮጌ ጋሻ አለ:
በጋሻዉ ትክክል መሬት ላይ የቆመ:
ረዥም ጦር አለ ትንሽ ያዘመመ:
ከዱልዱሙ ጦር ጎን ትንሽ ፈንጠር ብሎ:
ከሩቁ ይታያል የዉሃ መያዣ ኮዳ ጉቶ መስሎ:
ከእዚህ በስተቀር :
በዚያ ሰፊ ቤት ዉስጥ ምንም እቃ አልነበር::
ከሁሉም
ከሁሉም ሌባዉን ያጓጓዉ
በድር ተሸፍኖ የተንጠለጠለዉ
ባለ እጀታ ጋሻዉ
ለማዉረድ ሲሞክር
አልሆንልህ አለዉ በቁመቱ ማጠር
ታዲያ
ጋሻዉ እጀታ ላይ ያንን ጦር ሰክቶ
መሬቱ ላይ ጣለዉ በሀይል ጎትቶ
ከእግሩ ሸብረክ ብሎ
የጋሻዉን ጀርባ በቀኝ መዳፉ እየወለወለ
በደንብ አስተዋለ
ከጀታዉ ጎን ላይ እንዲህ የሚል ጽሁፍ አለ
‹‹ሰዉ.......
ኖረ ከተባለ?
ስለምን?
ስለማን?
ከማን ተጣጣለ?››
ይላል
ሽፍታዉን ገረመዉ
ጋሻ
ከመመከቻነት ከዉጊያ ባለፈ
ዘመን የሚሻገር መልዕክት እንዳቀፈ
ተረዳ
ከድሮ ባህሪዉ ከዘራፊነቱ ከግብሩ የራቀ
ሀሳብ ልቡ ገብቶ ብዙ ተጨነቀ
ዉስጡ እየከጀለ ሌላም ጽሁፍ እንዳለ
ያንን ትልቅ ጋሻ መወልወል ቀጠለ

ከጋሻዉ ጠርዝ ላይ
አረንጓዴ ቢጫ ባለ ቀይ ጥለት
ከጥለቱ መሀል እንዲህ የሚሉ ቃላት
‹‹ይህስ መመከቻ
ማጥቂያን መመልከቻ››
ይላል
ሌባዉ
ግራ ገባዉ
ምን ማለቱ ይሆን?
ጋሻ ጦማር ሲሆን?
አለ


#ይመልሱ ይሸለሙ

ታዲያ በዚህ ጊዜ
ማጥቂያ የሚለዉ ቃል መንገዱን ሲመራዉ
ጦሩን ሳብ አረገዉ
በእጁ እየዳበሰ ከጦሩ ጫፍ ሲደርስ
ደም ሌላ ስንኝ ሌላ የፊደል ቅርስ
‹‹ማን ወዶ ደም ያፍስ ህይወቱን ይገብር
ህመም ኖሮት እንጂ እናት ስትደፈር
ይሄን ያልተረዳ
ዉሃ ብቻ አለበት ባነገተዉ ኮዳ››
የሚል

ለዚህ ዘራፊ ልብ ለያዘዉ አእምሮ
ዉስብስብ ሆነበት ይህ ቃል ተጨምሮ
ራመድ እያለ ከኮዳዉ ተጠጋ
ዉስጡ ምን እንዳለ ማየት እየጓጓ
ኮዳዉን
በግራ እጁ አነሳዉ
ባፉ ዘቀዘቀዉ
እጅግ የረጋ ደም ከዉስጡ ፈሰሰዉ
ዘራፊዉ ክዉ አለ
እንዴት ሰዉ የሰዉ ደም ይጠጣል? እያለ
ብዙ አሰላሰለ
ከኮዳዉ ማበቻ ቆዳ ተጠቅልሏል
ጥቅልሉን ሲፈታዉ ሌላ ስንኝ ይዞአል
ስንኙም በደም የተጻፈ
የሚከተሉትን ቃላቶች ያቀፈ
‹‹ይህ ደሜ
ለስሜ
አጥንቴ
ለእናቴ
ስጋየ ከኔዉ ቤት
ቢያርፍስ ምን አለበት?››
ይላል

እያገላበጠ ኮዳዉ ላይ ቢያማትር
ሌላ ቃላት የለም ከነዚህ በስተቀር
ይበልጥ ግራ ገባዉ
ጦርና ጋሻዉን ደግሞ አስተዋላቸዉ
ምንም ጽሁፍ የለም
ታዲያ በዚህ ጊዜ
ይህን እንቆቅልሽ እያሰላሰለ
የቤቱን ክፍሎች ሁል ማሰሱን ቀጠለ
ምኝታ ቤት ሲደርስ በድንገት ቀጥ አለ
ያየዉን ለማመን እጅግ ተቸገረ
ፈራ እግሩ ራደ ልቡ ተሸበረ
አረንጓዴ ቢጫ ቀይ
ምንጣፍ ያለዉ አልጋ ተዘርግቷል
ከአልጋዉ ላይ
የሞተ ሰዉ አጽም በክብር ተኝቶአል
ከአጽሙ ራስጌ
አንድ የብራና ጽኁፍ በአልበም ዉስጥ ተቀምጧል
ጽሁፉ እንዲህ ይላል
ልጀ ሆይ!
አደራ አትረብሸኝ!
ይበቃል ካዎቅኸኝ!
ነገር ግን
ስለ ትናንትና ማንም ከጠየቀህ
አንተን አሳያቸዉ ስለኔ ተናግረህ።
ላሁኑ!
ይበቃል ካዎቅኸኝ
ግን እንዳትረብሸኘኝ
ይላል
ይሄንን አንብቦ ልክ እንደቸጨረሰ
ቤቱን ለቆ ወጣ የጉንጩን ላይ እምባ በእጆቹ እያበሰ።

በዉብአረገ አድምጥ



በፎቶግራፍ ዘርፍ አሸናፊ ምስል
ፎቶ :- የማነ ተሾመ
ሀመር ቡስካ
ለኢቫንጋዲ ምሽት ዝግጅት ላይ የተነሳ

# የተሻለች ዛሬን ዘርተን የተስተካካለ ነገን እንጨድ

በሕሊና በቀለ

ባለፈው ወንድሜ ፌስቡክ ላይ ያገኘውን ጽሁፍ አበበልኝ፡፡ ጽሁፉ እንዲህ ይላል ‹‹የ60ዎቹ እና የ70ዎቹ ልጆች እየጨሱም ቢሆን ትምህርት ላይ ጀት ነበሩ፤ የ80ዎቹ ልጆች ብሄራዊ ውትድርና ሽሽት በቦሌም በባሌም ስደት ላይ ነበሩ፤ የ90ዎቹ ልጆች ግን በኛ ላይ ሙድ እንደያዙ እስከአሁን አሉ፡፡ ››
ይህን ሲያነብልኝ በጣም ብዙ ነገሮችን እንዳስብ እና እንድጠይቅ አደረገኝ፡፡ እኛ የአሁኑ ትውልድ ምን እያረግን ነው? አገራችንን አሁን በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው ፣ በማህረሰባዊው ዘርፍ  እየመሯት ካሉት ሰዎች የተሻለ እንጂ የባሰ ላለመሆን ምን ያህል  እየተዘጋጀን ነው? ፣ ከኛም አልፎ እኛን ለሚተኩን መጪው ትውልድ የሚኖሩበትን አካባቢ በማስተካከል ዙሪያ ምን ያህል የድርሻችንን እየተወጣን ነው?  ከትችት እና በየማህበራዊው ሚዲያ ላይ ሃሳባችንን ከመግለጽ ባለፈ የምናምንበትን ሃሳብ እውን ለማድረግ ምን ያህልስ እየለፋን ነው?!
አሁን ላይ በጣም ብዙ ወጣቶች በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይም ይሁን በተለያዩ መድረኮች ላይ ጠንካራ አቋማቸውን በመግለጽ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ በጣም ትልቅ ለውጥ ነው ምክንያቱም የተለያዩ ንቅናቄዎችን እና የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን ማዘጋጀት ማህበረሰቡ እንደ ችግር ያላየውን፣ አይቶም እንዳላየ ያለፈውን ነገር እንዲያስተውለው ስለሚያደርግ ነው፡፡ ይህ ብቻ ግን ጥቅም የለውም፡፡      ለምሳሌ ኢትዮጲያ ውስጥ የመረዳዳት ባህላችን እየጠፋ ነው ካልን፤ እኛ ይህንን ችግር ለመቅረፍ በአቅማችን የተራቡትን እያበላን ነው ወይ? ፣ ሙያ አስተምረን ወደተሻለ ደረጃ እንዲደርሱ እየረዳን ነው ወይ?፣ መንገድ ላይ ተገቢ ያልሆነ ነገር ስናይ ምላሻችን ምንድን ነው/ የሚሉትን ተያያዥ ጥያቄዎች መመለስ መቻል አለብን፡፡ የሃገራችን ኢኮኖሚ እየወደቀ ነው፣ ኑሮ አየተወደደ ነው ብለን ስንተች የሃገር ውስጥ ምርቶችን በመግዛት ኑሮአቸውን ለማቅናት የሚለፉ ወገኖቻችንን ረድተናል ወይስ ከውጪ የመጣ ልብስ ነው፣ ጫማ ነው  እያልን አጊጠናል? የሚለውን ጥያቄ አብሮ መመለስ ግዴታችን ነው፡፡
 ዳንኤል ክብረት በአንድ ጽሁፉ ስለአማርኛ ቋንቋ ሲያወራ ‹‹አማርኛ ቋንቋ ሜንቴን (Maintain) ለሚባለው እንግሊዝኛ ቃል ቀጥተኛ ትርጉም የለውም፤ ትንሽ ቀረብ የሚለው ቃል መጠገን ነው›› ይላል፡  አንድ ነገር ለመጠገን ደግሞ መበላሸት አለበት፡፡ ሳይበላሽ ጠብቆ ማቆየት የሚባለው ነገር ግን በኛ ሃገር ስላልተለመደ ነው መሰለኝ ቃል እንኳ የለውም፡  እኛም የአሁኑ ትወልድ ልጆች ከመተቸት አልፈን ያለውን ጥሩ ነገር ጠብቆ፣ የተበላሸውን ጠግኖ፣የራሳችንን አሻራ አክሎ ማለፍ የሚለውን አስተሳሰብ ለማምጣት መንቀሳቀስ መጀመር አለብን፡፡
 ቤተሰቦቻችን እነሱ ካለፉበት የህይወት ጎዳና በተሻለ መልኩ እንድንኖር የሚችሉትን ያክል ሞክረዋል፡፡ እንዲኖረን የምንፈልገውን ህይወት ማምጣት ግን የኛ ሃላፊነት ነው፡፡ የምናወራውን እንኑረው፡፡ እንደግለሰብም እንደ ሃገር ተረካቢም የሚጠበቅብንን እንወጣ፡፡ የተሻለች ዛሬን ዘርተን የተስተካካለ ነገን እንጨድ!!



አናናስ ግርማይ
የሥነ-ማህበረሰብ ባለሙያ
britanitam@gmail.com


# እንኳን አደረሳችሁ


ይህ አባባል ትልቅ መሆኑ የሚገባን ባለፈው ዓመት ከኛጋር የነበሩ ዘመዶቻቻን፣ ጉደኞቻችን ወይም ወገኖቻችንና የምናውቃቸው ሰዎች በሞት ምክንያት ለአዲሱ ዓመት አለመድረሳቸውን ስናይ እና  እኛ ደግሞ በህይወት ተርፈን ስለመኖራችን ዋጋና ክብር ስጥተን ደስታችንን ለመግለጥ የምንጠቀምበት መሆኑ ነው። ታዲያ አበው የተውልንን ባህላዊ አባባል "እንኳን አደረሳቸሁ!"  እየተባባልን ከዘመድ አዝማድ ጋር በደስታ በዓሉን ማሳለፍ በጣም አስፈላጊ ነዉ። ግን ግን አዲስ ዓመት ስለመጣ ብቻ ህይወታችን አዲስና ውጤታማ ይሆናል ብሎ ማሰብ ችግር አለበት እላለሁ። ምክንያቱም በህይወታችን የሚመጣ ለውጥ በእጃችን እንጂ በዘመኑ መለወጥ ላይ አለመሆኑ ግልፅ መሆን ስለአለበት። ይህን በተመለከተ አንድ አባባል ትዝ አለኝ "If you want to have something you have never had, do something you have never done" "በህይወትህ ኖሮህ የማያውቅን ነግር ማግኘት ከፈለግህ አድርገኸው የማታውቀዉን ነገር አድርግ" ይላሉ። ታዲያ እዚህ ላይ አዲስ ነገር በህይወታችን እንዲሆን ከፈለግን ይህን አዲስ ነገር የምናገኘዉ በአስማት ድንገት በሚመጣ ትዕንግርት ሳይሆን በእኛ ዉስጥ ኖሮ አስበንበትና መክረንበት በምናደርገዉ እንቅስቃሴ መሆኑን መረዳት ስንችል ነዉ። ሌላው ባለፈው አዲስ ዓመት የገባናቸው ቃሎችና ያስቀመጥናቸው እቅዶች ለመተግበር ትዕግስት፣ ትጋትና ቁርጠኝነት በማጣት የዛሬን ጉልበትና ብቃት ለነገ ጥበቃ አሳልፈን በመስጠት ብዙ አዲስ ዓመቶች አልፈዋል።


ኤክሃርት ቶል (Eckhart Toll) The Power of Now, በሚለው መፅሐፋቸው "it is not uncommon for people to spend their whole life waiting to start living"። ሰዎች የህይወት ዘመናቸዉን ሁሉ መኖር ለመጀመር በመጠበቅ ጊዜያቸዉን ማሳለፍ የተለመደ ነው" ይላሉ። ይህም ማለት ብዙውን ጊዜ ገና ከፊታችን በሚመጡ ጊዝያቶች እንዲሆኑልን የምንፈልጋቸው ነገሮች እስኪሆኑ ድረስ እየኖርን ስለማይመስለን ዛሬን አባክነን ባዶ ነግን እንቀበላለን ። ታዲያ የዛሬዉ መልእክቴ እንኳን ወደ ዛሬ ሙሉነት ከነተግዳሮቱ በሰላም አደረሳችሁ እያልኩኝ ከንቱ ምኞት ከመመኘትና በይሆናል ከመጠበቅ ወደ ተግባር እንግባ እላለሁ።

በአቤቶ በሀይሉ

# የራሳቸው ዘመን አቆጣር ስላላቸው ሀገራት ምን ያህል ያውቃሉ?

















ዮናስ ጋ/ማርቆስ
lijyoha@Gmail.com



ሰላም እንደምን አላችሁ የቅንድል ዲጅታል መጽሔት ቤተሰቦች።እንኳን ለ፳፻፲፫ አዲስ አመት በሰላም አደረሰን። መቼም ለአዲሱ አመት የተለዩ እቅዶችን አቅዳችሁ ይሆናል።በእቅዳችሁ ውስጥ እንድታስገቡልኝ የምፈልገው አንድ እቅድ አለ።ቢያንስ በቀን ውስጥ ፩ ሰዓት የንባብ ጊዜ እንዲኖራችሁ እና በወር አንድ መጽሀፍ የመግዛት ልምድ ማዳበርን ከእቅዳችሁ ውስጥ አንዱ እንድታደርጉት ነው።ሁሌም ቢሆን ለምታቅዱት እቅድ ታማኝ መሆን አለባችሁ።ለራሱ ያልታመነ ለሌላው አይታመንምና።
#መልካም የንባብ ጊዜ!





## ሀሰተኛው በእምነት ስም

ደራሲ:አለማየሁ ገላጋይ
ይዘት: ልቦለድ
ገጽ ብዛት: 302
ዋጋ: 180ብር





## ጥቋቁር አናብስት

ደራሲ: ሩዶልፍ ኬ ሞልቬር
ተርጓሚዎች:ቴዎድሮስ ሸዋንግዛው እና ኤፍሬም ጀማል አብዱ
ይዘት: ግለ ታሪክ
ገጽ ብዛት: 418
ዋጋ: 250 ብር




## ጠበኛ እውነቶች

ደራሲ: ሜሪ ፈለቀ
ይዘት: ልቦለድ
ገጽ ብዛት: 252
ዋጋ:120 ብር




## መከረኞቹ

ደራሲ: ቪክቶር ሂዩጎ
ተርጓሚ:ሳህለስላሴ ብርሀነ ማርያም
ይዘት: ልቦለድ
ገጽ ብዛት 545
ዋጋ: 250 ብር



# እራሳችንን ይቅር እንበለው! ይቅርታን ከጠየቀ!

በዶ/ር ቢኒያም ግርማቸው

ወቀሳ ለማንም ጠንካራ ነኝ ለሚል ሰውም ከባድ ሸክም ነው። ሌሎች ሲወቅሱን፤ ከጥፋታችን በላይ ሊቀጡን ሲሞክሩ ምን ይሰማናል? ወቀሳ እረፍት የሚነሳ፤ የሚያሸማቅቅ፤ ዝቅተኝነት እንዲሰማን የሚያደርግ ስሜት ነው።የሚገርመው ብዙን ጊዜ ከሌሎች ሰዎች ዘንድ የሚመጣውን ወቀሳ ነው እንጂ፤ እኛ በገዛ እራሳችን ላይ የምናዘንበውን ወቀሳ አስተውለነው አናውቅም። ሃዘናችን በብዛት የሚመነጨው እራሳችንን ይቅር ካለማለት ነው። ለስህተታችን ይቅርታን ስንፈልግ፤ ሌሎች እንዲምሩን እንጂ ከራሳችን መምጣት ስለሚገባው ምህረት አናስብበትም። ኸረ እንደውም አንዳንዶቻችን እራሳችንን ይቅር ስለማለት ምንም አይነት ግንዛቤው የለንም። ያለናንተ መኖር የማይችል ብቸኛ ልጃችሁ ለስህተቱ ይቅርታን እየለመነ ይቅርታችሁን ብትነፍጉት ምን ያህል ህሊናውን እንደሚያቆስለው መገመት ከባድ አይደለም። ማንም ሰው በአለም ላይ ከሁሉ አስበልጦ ከሚቀርበው ሰው ይቅርታን እንደመነፈግ የሚያስጨንቀው እና የሚረብሸው ነገር አይኖርም። ለዚህ ነው እኛም ትላንት ለሰራነው ስህተት፤ ላጠፋነው ጥፋት፤ ለበደልነው በደል ከሌሎች ይቅርታ እኩል እራሳችንን ይቅር ማለት ሊለምድብን የሚገባው።ለወቀሳ ሌሎች ሰዎች ከበቂ በላይ ናቸው፤ እኛም ከሌሎች ጋር ተደርበን እራሳችንን ብቸኛ አናድርገው። አንዳንዶቻችን የሰራነው ጥፋት ለይቅርታ የሚከብድ እየመሰለን፤ በትላንት ስህተታችን ታስረን ዛሬንም ፤ ነገንም በጨለምተኝነት እናሳልፋለን። እኔ በበኩሌ ለይቅርታ የሚከብድ በደል ያለ አይመስለኝም። ምንም ያህል ስህተትን ብንሰራም፤ እስትንፋሳችን እስካለ ድረስ ከበደላችን በላይ ገዝፎ የሚታይ መልካም ስራ ለመስራት እድሉ አለን። አብዛኛዎቻችን ግን ለራሳችን ይቅርታ ስለምንነፍገው፤ መልካምነታችን እንዳያቆጠቁጥ አፈሩን በጸጸት እናደርቀዋለን። ጸጸት ከስህተት እስካረመን ድረስ መልካም ስሜት ነው፤ ነገር ግን ልኩን አልፎ ከንቱ ቢስነት እንዲሰማን ካደረገን ግን ጸጸት ሳይሆን ይቅርባይነትን መነፈግ ነው።

እስቲ አስቡት አንድ ሰው ትላንት ለሰራው ስህተት እስከመቼ ነው መወቀስ ያለበት? ይቅር አለመባልን በሌላው ላይ እራሱ ስናስበው ይከብዳል። ነገር ግን ባለማውቅ ሁላችንም እራሳችን ላይ የምንፈጽመው በደል ነው። በዚህ ምድር ላይ በይቅርታ የማይነጻ በደል፤ በንጹህ መጸጸት የማይታጠብ የልብ ቆሻሻ የለም። በትላንት ህይወታችን ምንም አይነት ሰው ብንሆንም፤ ዛሬን ነጽተን ለመኖር የሚያግደን አንዳችም ነገር የለም።በቅድሚያ ግን ከማንም በፊት እኛ እራሳችን ይቅር ልንለው ይገባል። መነሻችን ሳይሆን መድረሻችን ትርጉም እንዳለው መረዳት አለብን።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጌታችን ሲሰቀል አብሮ በቀኝ የተሰቀለው ፊያታዊ ዘየማን ምንም እንኳን እድሜውን በሙሉ በበደል እና በውንብድና ቢያሳልፍም፤ ነፍሱ ከስጋው እስክትላቀቅ ድረስ ለመልካም ምግባር ያልታደለ ቢሆንም፤ ለሞቱ ደቂቃ ሲቀረው በፈጣሪ ይቅር ባይነት ከማንም ቀድሞ ገነት ገብቷል። ይህንን ሚስጥር የሚረዳ ሰው እራሱን በጸጸት ከጥቅም ውጪ አያደርግም። ከንቱነት የሚሰማን ሁሌም እራሳችንን ከልክ በላይ ስለምንወቅሰው እና ይቅርታን ስለምንነፍገው ነው። የትላንት ቅሻሻችን ዘላለማችንን የማይለቅ ጠባሳ አድርገን ስለምንቆጥረው፤ ለመልካም ምግባር ያልታጩን አድርገን እራሳችንን እንቆጥራለን።እውነቱን እናውራ ካልን፤ ሰዎች ከማይረባ ህይወት እራሳቸውን ለማላቀቅ ያስቡና አንዴ ተጨማልቄያለው በማለት ለራሳቸው ይቅርታን በመንፈግ ባሉበት ዘቅጠው ይቀራሉ።ለምሳሌ የቡናቤት ሴት መንፈሳዊ ሰው ለመሆን ብትፈልግ እንኳን፤ እራሷን ይቅር ማለት ይከብዳትና ለመልካም ስራ የማትበቃ እየመሰላት በጀመረችው የስህተት ጎዳና ትቀጥልበታለች።በመንፈሳዊውም ሆነ በአለማዊው መልኩ ብንቃኘው እራሳችንን ይቅር ማለት ከትላንት ስህተት እራሳችንን ለማላቀቅ የመጀመሪያው እርምጃ ነው።ሌሎች ሰዎች ይቅርታቸውን ቢነፍጉን እንኳን እኛ እራሳችንን ይቅር በማለት የህሊናን እረፍት ማግኘቱን መልመድ አለብን።

ሰው የተናገረውን ቃል መልሶ ሊውጠው አይችልም፤ የሰራውን ስራ፤ ያጠፋውን ጥፋት ወደኋላ መልሶ ሊሰርዘው አይችልም። ብቸኛው ነገር በይቅርታ እራስን ማጽዳት ነው። ስለዚህ ሌሎች ይቅርታን ከነፈጉን የኛ ችግር ሊሆን አይችልም፤ በእርግጠኝነት የምናምነው ፈጣሪ ይቅር ይለናል፤ምክንያቱም ይቅር ባይነት ባህሪው ስለሆነ።ከሌሎች ወቀሳ ለማምለጥ ብቻ አንሞክር፤ እረፍት የሚነሳው ትልቁ ወቀሳ የራሳችን የህሊና ጩኸት ነው።ይቅርታ ለጠየቀን ሁሉ ይቅርታችንን አንንፈገው፤ ለራሳችንም ጭምር!!!ይቅርታ ለጠየቅ ይቅርታ ይደረግለት!!ሌሎች መሰል አስተማሪ ፅሁፎችን "ሰው ሁን ከሰውም ሰው ሁን" (EthioBini) ላይ ያገኛሉ።



Mh
GRAPHICS
Feel The Fascination!

## በልዩ ጥራት የምንሰጣቸው አገልግሎቶች

- ሎጎ ዲዛይን
- የዲጂታል መፅሔት ዲዛይን
- የዝማሬ ፖስተር
- የአልበም ከቨር
- የልደትና ሰርግ ካርዶች
- ቢዝነስ ካርድ
- የባነር ዲዛይን
- የፍላየርና የብሮሸር ዲዛይን
- የቲሸርት ዲዛይን
- የፊልምና የማስታወቂያ ፖስተር
- እና ሌሎች

ይደውሉ (+251) 920019699

በማህበራዊ ገፆች ያግኙን

TELEGRAM @MHGRAPHICS
INSTAGRAM @MHGRAPHICSHD




# እራስዎን እና ቤተሰብዎን ከኮሮና ቫይረስ ይጠብቁ !

## ባለመዘናጋትዎ ህይወት ይታደጋሉ !

● ኮሮና መድሀኒትም ሆነ ክትባት ያልተገኘለት ገዳይ ቫይረስ ነው

● ፊትዎን ባልታጠበ እጅ ባለመንካት ፣ ሰው በተሰበሰበበት ቦታ ባለመገኘት ፣ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ በአግባቡ በማድረግ ከቻሉም ከቤት ባለመውጣት ራስዎን ይጠብቁ!


ቅንድል ዲጂታል መፅሔት

KENDEL DIGITAL MAGAZINE

#ሳይ ቴክ



ለዓለም ክንፈ
lexkinfe5@gmail.com




# በ2012 በሳይንስና ቴክኖሎጂው ዘርፍ የተተገበሩ አበይት ክንውኖች

ጊዜ… ግን ለእርስዎ የጊዜ ትርጉም ምንድነው? አዲስ ዓመትንስ እንዴት ይገልፁታል? እውን ነው አዲስ ዓመት ለአብዛኛው ሰው የአዲስ ጅማሮ፣ የተስፋ ፣ የጥንካሬ እና የላቀ ብልጽግና ምልክት ነው። በሳይንሱ መነፅር ካየነው ግን ጊዜ የምንለው ነገር አንፃራዊ ነው። የሰው ልጅ የመሬትን ፀሐይን ተከትሎ የመዞር ዑደት መሰረት በማድረግ መሬት በአንፃራዊነት ከተነሳችበት ቦታ ዞራ ስትደርስ ያለውን ልዩነት አንድ ዓመት ብሎ ስያሜን እና ትርጉምን በመስጠቱ ይኸው አሁን ወደ ቀጣዩ ዓመት 2013 ተዘዋውረናል። እኔም ባለፈው ዓመት አበይት ይሆናሉ ያልኳቸውን ክንውኖች ከሳይንሱ እና ቴክኖሎጂው ዓለም ሸክፌ አቀረብኩላችሁ።

## የኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሳተላይት ምጥቀት

የ2012 ዓ.ም ትውስታችንን የምንጀምረው ባለፈው ዓመት ለሃገራችን በስፔስ ቴክኖሎጂው ዘርፍ ትልቅ እርምጃ በሆነችው የኢቲአርኤስኤስ 1 ምጥቀት ነው። ሳተላይቷ ማይክሮ ሳት ከሚባሉት የሳተላይት ዓይነቶች የምትመደብ ሲሆን ከመሬት በአማካይ 700 ኪሎሜትር ላይ በመሆን ምድርን በመዞር ኢትዮጵያን ደግሞ በአራት ቀን አንድ ጊዜ በመቃኘት የአየር ንብረት፣ የአፈር አይነትን፣ ድርቅ፣ የደን ሽፋንን እንዲሁም ሌሎች ጠቃሚ የግብርና መረጃዎችን እንጦጦ ወደሚገኘው ሳተላይት መቆጣጠሪያ እና መረጃ መቀበያ ማዕከል እየላከች ትገኛለች። ይቺ ሰው ሰራሽ ሳተላይት በአማካይ 70 ኪሎ ግራም መጠነ ቁስን የምትመዝን ሲሆን ከሳምንታት በፊት የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ኢንቲትዮት ባወጣው መረጃ መሠረት በመጪው ታህሣስ ወር መጨረሻ ላይ በመጠሪያ ስማቸው የመሬት ምልከታ ሳተላይ ከሚባሉት የሳተላይ ዓይነቶች የምትመደብ እና መረጃን በመሰብሰብ ከETRSS1 የተሻለ ጥራት ያላትን ሳተላይትን ለማስወንጨፍ በዝግጅት ላይ እንዳለ አሳውቋል።

## በመሳሪያ ስርዓት ታዋቂ የሆነው Windows 7 ይፋዊ መዘጋት

ማይክሮሶፍት በፈረንጆቹ የዘመን ቀመር ጥር 14፣ 2020 ላይ ሁላችንም በተለይም በኢትዮጵያ እስካሁን በስፋይ ግልጋሎት ላይ ይገኝ የሚገኘውን Windows 7 የመሳሪያ ስርዓት End of Life አውጇል። ይህም ማለት ካሁን በኋላ ይህን የመሳሪያ ስርዓት ለሚጠቀም ማንኛውም ኮምፒዩተር Microsoft ምንም ዓይነት የሙያዊ ድጋፍም ሆነ የደህንነት ጥበቃን አያደርግም ማለት ነው። Microsoft በመግለጫው የWidows Xp ምትክ ሆኖ ወደ ገበያ በ2010 ላይ የተቀላቀለውን windows 7 ከዐሥር ዓመት የግልጋሎችት ድጋፍ በኋላ መዝጋቱን ሲያሳውቅ ተጠቃሚዎች ወደ ቀጣዮቹ የዊንዶውስ ስሪቶች ማለትም Windows 8.1 እና Windows 10 የመሳሪያ ስሪታቸውን እንዲያዘምኑ ምክራቸውን ለግሰዋል።

## የኮሮና ቫይረስ የመጀመሪያ ግኝት

ኖቬምበር 17፤ 2019 ለመጀመሪያ ግዜ በቻይና ሁቤይ ግዛት ሁዋን ከተማ እንደተገኘ የሚነገርለት የSARS-Cov-2 ቫይረስ በጥቂት ወራት ውስጥ ይህ ፅሑፍ እስከተፃፈበት ግዜ እንኳን 27.6 ሚሊዮን ሰዎችን በዓለም ዙሪያ ሲያጠቃ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ 900 ሺህ የሚሆኑት ህይወታቸው ሲያልፍ ከ18 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች አገግመዋል። ወደ ሃገራችን ኢትዮጵያ ስንመጣ ደግሞ የመጀመሪያው የኮሮና ቫይረስ ኬዝ ከተገኘበት ከመጋቢት ወር መጀመሪያ አንስቶ እስካሁን ወደ 60 ሺህ የሚጠጉ የቫይረሱ ተጠቂዎች ሲገኙ ከእነዚህ ውስጥ ወደ 1000 የሚጠጉ ዜጎች ለህልፈተ ህይወት የተዳረጉ ሲሆን ከ22 ሺህ በላይ ሰዎች ደግሞ ከበሽታው አገግመዋል። ኮቪድ 19 የሃገራትን የጤና ስርዓት ብቻ ሳይሆን ምጣኔ ሃብታዊ፣ ማህበራዊ ቀውሶችን በእጅጉ እያስከተለ ያለ በሽታ ሲሆን ምናልባትም ዓለማችን ባለፊት 100 ዓመታት ካጋጠሟት ተግዳሮቶች በግንባር ቀደምትነት የሚሰለፍ ነው። በዚህም ምክንያት አሁንም ቢሆን ይህንን ገዳይ በሽታ የጤና ባለሙያዎች በሚሰጡን ምክር መሰረት ተጠንቅቀን እንለፍ ስንል የዚህ መፅሔት አዘጋጆች ጥሪያችንን ለማስተላለፍ እንወዳለን።

## ስፑትኒክ ቪ

ይህ የሮኬት ስያሜ የሚመስል ስምን የያዘው የኮሮና ቫይረስ ክትባት በሩሲያው ፕሬዚደንት ቭላድሚር ፑቲን በፈረንጆቹ የዘመን ቀመር ኦገስት 13 ይፋ የተደረገ ሲሆን ፕሬዚደንቱ የክትባቱን ተአማኒነት ለመጨመር አስበውም ይመስራል በሴት ልጃቸው ጭምር ላይም እንዳስሞከሩት ተናግረዋል። “ልጄ ክትባቱን ከተወጋች በኋላ ትንሽ ራስ ምታት ነበራት፤ ከላ በኋላ ግን ያሳየው ውጤት አመርቂ ነበር” ሲሉ የገለጹት እኚህ ሰው፤ እንደ እርሳቸው ግምት በቀጣዮቹ ወራት ለሃገራቸው ህዝብ ብሎም በቀጠናቸው ለሚገኙ ሃገራት ይህንን ክትባት ለማዳረስ የክትባት ማምረት ሂደቱ እንደተጀመረ ነው የገለጹት። ይህ የኮቪድ 19 ክትባት ተዓማኒነቱን ከግምት ውስጥ ያስገቡት ምዕራባውያኑ ከዚህ በተቃራኒ ለቫይረሱ ሁነኛ መፍሄ አይደለም እያሉ ይገኛሉ። እንደነርሱ እምነት ክትባት ለማግኘት እና ለማሰራጨት እስከ ፈረንጆቹ 2022 አጋማሽ መጠበቅ ያስፈልጋል። ነገር ግን ብራዚልን የመሳሰሉ በዚህ ተህዋሲ ክፉኛ የተጠቁ ሃገራት በፈረንጆቹ 2021 አጋማሽ ላይ ክትባቱን ከራሺያ ወስደው ለህዝባቸው ለማጋራት እየተደራደሩ ይገኛሉ።

## ኒውራሊንክ

ኒውራ ሊንክ የተባለው የፈጠራ ሃሳብ በስፔስ ኤክስ እና ቴስላ ባለቤት ኢሎን መስክ በ2018 ወደ ምርምር ከገባ በኋላ ነበር በሳምንታት በፊት የመጀመሪያ የሚባለውን ሙከራ በአሳማ ላይ ያደረገው። ኒውራ ሊንክ ምንድነው ቢሉ፤ በጣም ጥቃቅን የሆነ የኮምፒዩተር ማይክሮፕሮሰሰር ቺፕን ከሰው ልክ አዕምሮ ጋር በማዛመድ የሰው ልጅ እንደ ስልክ መደወል እና በይነመረብን በመጠቀም በአካሉ ላይ ለሚገጠሙ ማናቸውም ሰው ሰራሽ አካላት ትዕዛዝን ለመስጠት ታስቦ የተጠነሰሰ ፕሮጀክት ነው። ይህ ፕሮጀክት ዕውን ከሆነ የዚህ ከፀጉር ዘለላ የሚያሰው ማይክሮ ፕሮሰሰር በአዕምሮዋቸው ያስቀበሩ ሰዎች ከአቻዎቻቸው ጋር ሳይነጋገሩ ለመግባባት እንደሚችሉ ይታመናል። ነገር ግን ፕሮጀክቱ ጊዜ የሚወስድ ሲሆን ይህ ካምፓኒም የሰው ልጆች ላይ ሙከራን ለማድረግ እስካሁን ፈቃድ አላገኘም። ለዛም ነው ከላይ እንደተጠቀሰው ለመጀመሪያ ጊዜ በአሳማ ላይ ሙከራው የተጀመረው።


ምንጭ:- Cloudfont.net , euronews/ETRSS1








































ለበፊት እትሞች በቴሌግራም
@KendelM ያገኙናል